የሸናሻን ቋንቋ በቀላሉ መናገር የቻልሁት ያን ጊዜ ነበር።" አለ ገሞራው።

"ነጯን አብሾ አገኘኻት?" አለ ኄርማ የቅኔ ሊቅነቱ ከነጭ አብሾ የተወለደ መስሎት።

"የለም! ዳክሬ ዳክሬ ፍሬ አልባ ሆኜ ነው የተመለስሁ" አለ ገሞራው።

"የት ድረስ ፈልገኻት ነበር?" አለ ታሪኩ።

"ዐባይ ዳር ድረስ ነዋ!" ሲል አመጣው።

"ቅኔ ቤት ሳለን

"ጠላ ያለጌሾ።

ቅኔ ያለአብሾ" እያሉ ሲተርኩ እንሰማ ነበር። እኔም በእድሜዬ ገና ብላቴና እያለሁ የትምህርት መድኃኒት ለመውሰድ ታታሪ ነበርሁ። ከዚህ እሳቤ ተነሥቼ ነጭ አብሾ ፍለጋ ወደዚህ ሀገር መጣሁ። ከዐባይ ዳር ነጭ አብሾ ለመፈለግ ስመጣ የጉምዝ ሽፍቶች በየስፍራው እያስቆሙ አንገራገሩኝ። ያንን በመላ ለማለፍ ከቻግኒ ከመጡ የጤና ባለሙያዎች አንዱን የቡድን መሪ ቀረብ ብዬ "የቅኔ ተማሪ ነኝ" ወዲህ የመጣሁት ነጭ አብሾ ፈልጌ ነው። አሁን ግን





እንደልቤ መፈለግ አልቻልሁም። የዚህ ሀገር ወንበዴዎች እያስፈራሩኝ ነው። ከእኛ ጋር የመጣ ነው ብለህ ወደታች ዐባይ ውሰደኝ። ነጭ አብሾ ከተገኘች ለልጆችህ የትምህርት መድኃኒት አጠጣልኻለሁ አልሁት። ተስማማን። ያን ጊዜ ሽፍቶች የወባ መድኃኒት የሚረጩትን ያከብሩ ነበር። የወባ መድኃኒት ከሚረጩ የጤና ባለሙያዎች ጋር ስምምነት ፈጥሬ በዚህ በረኃ እንደልቤ ተንሸራሸርሁበት። የነጭ አብሾውን ጎሠሣም ገፋሁበት።" ካለ በኋላ

"ዶክተር ኄርማ ነገሩን ቀለል አድርገህ ተመልከተው። በቅኔ ቤት የተለመደ ነገር ነው። በተለምዶ ነጭ አብሾን የወሰደ የቅኔ ሊቅ ይሆናል የሚሉት ብሒል አለ። ከዚህ ብሒል ተነሥተን ነጭ አብሾ እንፈልግ ነበር። የነጭ አብሾ መፈጠሪያው ደግሞ ዐባይ ሸለቆ ነው እየተባለ እንደ ጉድ ይወራ ነበር። በዚህ ወሬ ለትንሽ ዓመታት ተጃጅያለሁ። ከመጀጃሌ የተነሣ ከዋሸራ ቅኔ ቤት እስከ ዐባይ ዳር በእግሬ ተጉዣለሁ። ዐባይ ዳር ከተማ ቢጤ ናት። ከእሷ እያደርሁ ዐባይ ለዐባይ ዘወር ዘወር እያልሁ በእግሬ እየተንከራተትሁ የወባ መድኃኒት ከሚረጩ ሰዎች ጋር ለዐራት ወር ፈልጌያት ነበር። ማግኘት ግን አልቻልንም። እሷ ስትጠፋ ያ የጤና ባለሙያ መስተፋቅር ካላመጣህ እያለ አስቸገረኝ። ሊገድለኝ እንደሚችል ጭምር አስጠነቀቀኝ። የበረኃ ሲሳይ ከመሆኔ



Scanned with CamScanner

በፊት መላ መመልመል ጀመርሁ:: ቅኔ ቤት ስመለ
እንደምሰጠው ቃል ገባሁ:: እሱም እውነት መስሎት ጊዜ
ሰጠኝ:: በመጨረሻ እሱን የቆላ ንዳድ አነደደችው:: ከሥራ
ባልደረባዎቹ ጋር ቀበርነው:: ከመስተፋቅሩ መቃብሩ ቀደመ::
" ብሎ ከተረከላቸው በኋላ መንገዳቸውን ቀጠሉ:: ከስዉሩ
ዓለም ለመድረስ ጉጉት ላይ ናቸው:: እንደከርታታ ኮከቦች
እየተንከራተቱ ነው::

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)





# ፲፫

## ዳንጉር ተራራ

ማለዳው ብዙ ደስ አይልም:: በተለይ ኄርማ ውስጡ ተከፍቷል:: በዛሬው ሌሊት ገሞራውም ቢሆን የጤና እንቅልፍ አላሳለፈም:: በሕልም የጀመረው እንቅልፉ በቅዠት አክትሟል:: ቢሆንም ከርታታ ኮከቦች ከስዉሩ ዓለም ለመድረስ መንከራተቱ ቀጥሏል:: ታሪኩ እንደ ልቡ እያወራ ነበር::

"እንደ ተዋነይ የሞቱን መግቻ ካገኘን በዚያው እንኖራለን:: ካልተመቸን ግን ወደመኻል ሀገር እንመለሳለን:: እኔ ከተመለስሁ ጎንደር መኖር ነው የምፈልገው::" አለ ታሪኩ::

"አዲሳባ አይሻልም?" አለ ኄርማ::

"አዲሳባ አየሩ መልካም ቢሆንም ወደፊት ለሰው ልጆች ጥሩ መኖሪያ አይመስለኝም:: ነገር-ዓለሙ ዝብርቅርቁ ወጥቷል:: ሁሉም ነገር ደስ አይልም:: ምስቅልቅሉ ወጥቷል:: የውስጡ ጉድ ብዙ ነው:: ከሊቅ እስከ ማይም ወደመዋዕለ ንዋይ ተወርውሯል:: ሊቃውንቱ ከቀለም ይልቅ ለገንዘብ ፍቅር አላቸው:: ያ መንፈስ ለእኔ አይመቸኝም:: ስለዚህ ጎንደር



Scanned with CamScanner

ይሻላል፡፡ እንገረብ አጠገብ ጎጆ ቀልሼ የጎንደርን ወረብና ዜማ እየሰማሁ ሞቴን እመርጣለሁ፡፡ ደግሞ ከስዋሬው ዓለም ወደ ጎንደር ከተመለስሁ ብዙ የማጠናቸው ምሥጢራት አሉ፡፡ አበሞ ጀምሮ የተዋቸውን የአቡሻህር ቀመራት ማጥናት እፈልጋለሁ፡፡ መጽሐፉ ወዴት እንዳለ ደርሸበት ስለሆነ በመጽሐፉ የምሠራው ነገር አለኝ፡፡ ወደ ጎንደር ነው መመለስ የምፈልገው፡፡ የጎንደር ቀለም ሲናፍቀኝ ከሚኖር እንገረብ ዳር ጎጆ ቀልሼ ብኖር እመርጣለሁ፡፡" አለ ታሪኩ፡፡

"ግድ የለም፡፡ ዋናው ከስዉሩ ዓለም ገብተን ከጥበብ ሴቶች የሞት መግቻውን ከጨበጥን በኋላ እንወስናለን፡፡" እያለ ታሪኩ ተምኔቱን ሲያወራ ገሞራው ሲከራከር ኄርማ በማስታዎሻው ሲከትብ በሽፍቶች ተከበቡ፡፡ ሁሉም ሽፍቶች ቀስት ቀስታቸውን አገንድረዋል፡፡ ፊታቸውን በጨርቅ ሸፍነዋል፡፡ ከእግራቸው ጫማ የላቸውም፡፡ ባዶ እግራቸውን ናቸው፡፡ ጥቂት ከፍ እንዳሉ ሽፍቶች ቀስት መወርወር ሲጀምሩ ሁለቱም ራዱ፡፡ ታሪኩ ከአንዲት ቁጥቋጦ ተሸጎጠ፡፡ ገሞራው ወደገደል ተንከባለለ፡፡ ሽፍቶቹ ከኄርማ ላይ መርዝ የተቀባ ቀስት ወደ ወዱበት፡፡ ዐይኑ ቀይ ቢጤ ጥላ ለበሰ፡፡ የቆመበት መሬት ዞረበት፡፡ አከታትለው ሲወጉት ሰማይ ጨለመበት፡፡ መርዙ ነበልባለ-እሳት አቀጣጠለበት፡፡ አቃስቶ ወደቀ፡፡ መርዝ የተቀባው ሹል ቀስት ሆዱን ተርትሮት ሲገባ





መንቀሳቀስ አቆመ፡፡ ሽፍቶቹ ሁለቱን ፍለጋ ወደፊት ገሰገሱ፡፡ ወደገሞራው ሲያሙለቁ ከገደሉ ሥር ተወሸቋል፡፡ አስተካክለው ሊዘረምጡበት የቀስቱን ደጋን ሲወድሩ ቀደማቸው፡፡ ከያዛት ውኃ ፉት ሲል ገደሉ ጨለመባቸው፡፡ ገሞራው ተሰወራቸው፡፡ ወደኋላ አፈገፈጉ፡፡ ገሞራው ጥግ ይዞ ይመለከታቸው ጀመር፡፡ እሱን ትተው ታሪኩን ማፈላለግ ጀመሩ፡፡ ታሪኩም የዋዛ ሰው አልነበረም፡፡ ታብርን ሲጠጣ ከፊታቸው ድርግም አለ፡፡ ዶክተር ኄርማን ገድለው እየፎከሩ ወደ ቆላው ወረዱ፡፡ ቀስታቸውን ከኄርማ ሆድ ላይ ሲነቅሉት ሰውነቱ ድርቅ ብሎ ነበር፡፡ ሕማም አልተሰማውም፡፡ ቀድሞ ሙቷል፡፡ ወንበዴዎች ወደ ቆላ ሲዘቀዘቁ ገሞራው እንባውን እያዘነበ ወደኄርማ ቀረበ፡፡ ታሪኩ ከወዲያ በኩል እየተፈጠረቀ ደረሰበት፡፡ አንገት ሳንገት ተቃቅፈው ቢያለቅሱም ውብ ዐይኑን ማየት አልቻሉም፡፡ ዶክተሩ ፈጽሞ ሙቷል፡፡ ሬሳውንና ማስታዎሻውን ተሸክመው ወደ ዳንጉር ሚካኤል ገዳም ደረሱ፡፡ ከገዳሙ በር ሲደርሱ መቃብር ቆፍረው አፈር አለበሱት፡፡ ገሞራው አብሬ ካልተቀበርሁ ዐይነት ልቅሶ ነበረው፡፡ ግብአተ መሬቱን ከፈጸሙ በኋላ ወደ ደቅ ማርያም አቀኑ፡፡ ደቅ ማርያም ሲደርሱ ከገዳሙ በር ቁጭ ብለው ሲያለቅሱ ሌሊቱ ወገግ አለ፡፡ ገዳማውያን መጥተው ተቀበሏቸው፡፡ በነጋታው ማለዳ ወደ ስዉሩ ዓለም ገሰገሱ፡፡

ገና የስድስት ሰዓት መንገድ ይጠብቃቸዋል። ሁለቱ የሲላ ዓለም ሰዎች ከምዕራባዊ ደቅ ገዳም ወደስዉሩ ዓለም ሲገሰግሱ ውስጣቸው በኀዘን ቆስሎ ነበር። ለጥበብ ሲንከራተቱ ሞት ጌጥ ቢሆንም የኄርማ ሞት ግን ሕልም ሆኖባቸዋል። ገሞራው እስከ ወዲያው ዶክተር ኄርማን የሚረሳው አይመስልም። ዶክተር ኄርማ የጀመረውን ጥናት በወግ በወጉ አድርጎ ከሕዝብ ጆሮ ለማድረስም ለራሱ ቃል ሲገባ ሰቅሰቅ ብሎ እያለቀሰ ነበር። ገሞራው ኄርማ የከተበውን ጥናት አንሥቶ ሲመለከት ከቆየ በኋላ

"ይህ ክታብ ዳጎስ ያለ መጽሐፍ ይሆናል። በመጽሐፍ መልክ ቢታተም ምን ይመስልሃል?" አለ ወደ ታሪኩ እየተመለከተ።

"መታተሙ መልካም ነው። ነገር ግን ለኄርማ ፍቅረኛ እንዳለችው ግልጽ ነው። አሁንም ድረስ ይመጣል ብላ ትጠብቀው ይሆናል። ድንገት በራድዮ ሲተረክ ብትሰማ ራሷን ታጠፋ ይመስለኛል። ይህንን አስበኸዋል?" አለ ታሪኩ።

"በቃ ይቅር። የእሷን ጉዳት ተወውና ይልቁንስ እናቱ ብትሰማ የአእምሮ በሽተኛ ትሆናለች።" ብሎ የኄርማን ማስታዎሻ ወደ አኮፋዳው ሰገሰገው። ከዚያም ራሱ ሊመልሰው የማይችለውን ጥያቄ አንሥቶ ድጋሜ ሰቅሰቅ ብሎ አለቀሰ።





ዶክተር ኄርማ በሠላሳ ዓመቱ ቢቀሰፍም የሃያ ሦስት ዓመት ፍቅረኛ እንዳለችው በተደጋጋሚ ሲናገር ገሞራው ሰምቶታል። ያን ሲያስብ ኄርማ ቀርቶ ራሱ ገሞራው ሙቶ ቢሆን ቀላል እንደነበር ገምቶ በራሱ ላይ ሞት ከፈረደ በኋላ "መቼስ ምን አደርጋለሁ። ሞት የተፈጥሮ ምሥጢር ነው። ከስዉሩ ዓለም ገብተን እንደ ተዋነይ እስክናወግዘው ይጫወትብን እንጂ መቼስ ምን እንባላለን።" ብሎ ማልቀሱን ቀጠለ። ውስጣቸው በኀዘን ስለ ተጎዳ እኽሉ አፈር አፈር እያላቸው መቅመስ አቁመዋል። ሲንከራተቱ በደረሰባቸው ሞት ደማቸው ፈልቷል። ቅስማቸው ተሰብሯል። ዶክተር ኄርማ በእነሱ ልብ ሕያው ቢሆንም ለዘለዓለም አሸልቧል።



Scanned with CamScanner

# ፲፬

## ከስጢሩ በር

ዐራት ዐይናውና ጠቢቡ ሖሪ ከደቅ በር ቁጭ ብለው ስጢሩና ገሀዱን ዓለም እየጠበቁ ሳለ ሁለቱ የቅኔ ተማሪዎች ዶክተር ጌርማን ተብረው ከመጀመሪያው ደቅ ማርያም አልፈው ከስጢሩ ዓለም ሥር ዱቅ አሉ። ደቅ እስጢፋ። ውጫዊ ጫካው በአረንጓዴ ተሞሽሯል። መዓዛው አእምሮ ይመስጣል። ማዶ ላይ የሕንዶች እርሻ ይታያል። ወደ ምሥራቅ ሲመለከቱ መኻል ሀገሩ ቁልጭ ይላል። ይህ ውጫዊ የደቅ እስጢፋ መልክአ ምድር ነው። ውስጣዊውን ግን ስጢር ነው። ወደ ፊት ሊመረመር የሚገባው፣ ደቅ እስጢፋ የተሰወረበት ዓለም ይሉኻል ይኸው ነው። የቅኔ ተማሪዎች ጥበብ ኀሠሣ የሚዳከሩበት ስጢሩ ዓለም ከገሞራውና ከታሪኩ ፊት ለፊት ቁጭ ብሏል። ተዋነይ መልአከ ሞትን ለማውገዝ የተመላለሰበት ደቅ እስጢፋ ከላይ ከላይ ብቻ ሲታይ ነፍስን በፍሥሓ ለማየ ለማያት ይሰቅላል።

ገሞራውና ታሪኩ በጌርማ ሞት ከቀቢፀ ተስፋ ደርሰው ወደ ስዋሬው ዓለም ሳይቀላቀሉ ለንብተው ነበር። አሁን ግን





እንደምንም ውስጣቸውን አሳምነው ከታብር ካመጧት ውኃ ለመጎንጨት ወሰኑ።

ውኃዋ ያች የጥበብ ምንጭ ታብር ናት። መጀመሪያ ማን መጠጣት እንዳለበት ለመወሰን ሲያመነቱ ቆይተው ዕጣ ተጣጣሉ። ለገሞራው ወጣለት። በኮዳ ከያዛት የተዋነይ ውኃ ተጎነጨ። ከጉሮሮ ስትወርድ እንደሙሉ ጨረቃ ወከክ ያለድንቅ ዓለም ጋር ተፋጠጠ። ራሱ ሲሰወርና በስዋሬ ካሉት ከዐራት ዐይናውና ከጠቢቡ ሖሪ ጋር ሲገጣጠም አፍታ አልፈጀበትም። ለጥቆ ታሪኩ ውኃዋን በቁሙ ፉት አላት። ስጢሩ ዓለም እንደጠራ ጨረቃ ወክክ አለ። አፈሩ ብርሃን ይተፋል። ሰማያዊ ብርሃን ከበባቸው። በሕይወት ገነት መግባት እንደማይቻል ስለሚያውቁ እንጂ በሕይወት ገነት የገቡ መስሏቸው ነበር። ዳሩ ግን ስዋሬ እንጂ የተፈጥሮ ለውጥ አልነበረም። ያው ገሞራውም ገሞራው ነው። ታሪኩም ታሪኩ ነው። በዚች ትንሽ ተራራ የሚኖሩ ደቂቀ-ተዋነይም ኢትዮጵያውያን ናቸው። ቋንቋቸው ግን ልዩ ነው። በቅዱሱ ቋንቋ ይናገራሉ። ግእዝ ሲናገሩ ጥፍጥናው ግሩም ነው። ከከንፈራቸው ሲቀዳ ልዩ ጣዕም አለው። ሰውነታቸውም ቀለል ቀለል ያለው ነው። ወደስዋሬ ተቀላቅሎ ከተመለከታቸው በቀር ይህንን ምሥጢር በቃል መግለጥ ይከብዳል። ዳሩ ግን ስዋሬው ሊስተባበል አይችልም። የስዋሬ

ዓለም መሆኑም እሙን ነው። ስዉሩ ደቅ እስጢፋ በከፊል ይኸውና!!

ገሞራው ወደ ዚህ ዓለም ሲገባ ከሐሳብ ያናጥበው የነበረው ሁከት ሙልጭ ብሎ ጠፋለት። ወደ ስዋሬው ዓለም ገብተው ግራ እንደተጋቡ ከወዲያ ማዶ አንድ ጥርሰ ፍንጭት ሰው እየሳቁ ከተፍ አሉ። ገሞራው ሰይጣን መስለውት በተደጋጋሚ ያማትብ ጀመር። መስጥመ አጋንንት ቢኖረው ኑሮ ያንን መጠቀም በወደደ ነበር። ሰውየው እየቀረቡ ሲመጡ ገሞራው ዐይኑን ማመን አልቻለም። ዐይኖቹን ከፍቶ መልሶ ደረገማቸው። ዐይኖቹን ሲከፈታቸው ሲከረችማቸው ሰውዬው በፍጥነት እየቀረቡ መጡ። ጠቢቡ ሖረ ነበሩ። እነሱ ዶክተር ጌርማን ቀብረው ከስዋሬው ዓለም በር ሲደርሱ እሳቸው በደመና ቀድመው ወደ ተዋነይ ዓለም ገብተው ከራርመዋል። ገሞራው እንደ ጨረቃ ወከክ ያለውን ዓለም ሲመለከት "በመኻል ሀገር የሚወራው ሁላ ትንሽ ትንሽ እውነታ ይኖረው ይሆን? ሰውን ወደአኽያነት ለውጠው ይሸጡታል። በሬ አድርገው ያርሱታል። ፈረስ አድርገው ይጋልቡታል።" የሚባለው በእኔ ሊደርስ? አታገልጠኝ ነው ማለት! አታጋልጠኝ! ጌታዬ ፈጣሪዬ አንተ ጠብቀኝ! እኔ አላውቅበትም። ጀርባዬን የፈረስ ጀርባ ሆኖ ቀይ ሽንኩርት ሲሸከም ከመኖር ጠብቀው። አጋሠሥ ፈረስ አታድርገኝ እያለ





በውስጡ ጸለየ። ከዚያም አንደበቱን ከፍ አድርጎ "ጌታዬ ሆይ! የሠራዊት ጌታ ወዴት አለህ? አታጋልጠኝ! ክርታታው ልጅህን አንተ ጠብቀኝ። ፖፓኤል! ፖፓኤል! ፓፓኤል! አለ። አምላኪየ አምላኪየ ወዴት አለህ? ወዴት አለህ? ማለት ነበር።

"ሰይጣን አይደለሁም። አታማትብብኝ፤ አትገዝተኝ። ክርታታው ሖረ ነኝ። ጎንጅ ደብረ ጥበብ ከዋርካው ዛፍ ላይ ሆነህ በደመና ስጫን ያየኸኝ ክርታተው ሖረ ነኝ። ታሪኩ አብሮ መጣ ማለት ነው? እንኳን ደኅና መጣችሁ!! ሰይጣንን ብትጠረጥሩ አይፈረድባችሁም ነበር። ዳሩ ግን ሰይጣንን ከመኻል ሀገር ጥላችሁት መጥታችኋል። ወደዚህ ዓለም ሰይጣን ገብቶ አያውቅም። ወደፊትም አይገባም።" ሲሉ በግእዝ ቋንቋ ከተናገሩ በኋላ ቀጠሉ።

"ወደዚህ ዓለም ማንም እንዳይገባ ወስነን ነበር። በወዴት በኩል አምሽልካችሁ ገባችሁ?" አሉ ጠቢቡ ሖረ።

ገሞራው የተዋነይን ውኃ እንደጠጡ በምልክት አስረዳቸው።

"እኔ ገሀዱን ዓለም እንጂ የስዉሩ ዓለም ጠባቂ አይደለሁም። ምን አገባኝ። ኑ ወዲህ። ከትልቅ ሰው ዘንድ ላድርሳችሁ።" እየመሩ ወደአንድ ሊቅ ወሰዷቸው። ካንዲት



Scanned with CamScanner

የዓለት ዋሻ በር ሲደርሱ አንድ ትልቅ መጽሐፍ አቅፈው ከልሙጥ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው በቁም ጽሑፍ የተከተበ ግዙፍ መጽሐፍ ከሚያነቡ ሊቅ ጋር ተጋጠሙ:: ዐራት ዐይናው ቀለሙ ዘቦሩ ሥላሴ ነበሩ:: በጠቢባኑ ዓለም ዓመታትን አሳልፈዋል:: በመኻል ሀገር ግን ሞታቸው እንጂ በሕይወት መኖራቸውን የሚያውቅ የለም:: በየቅኔ ቤቱ ሞታቸው በስፋት ተወርቷል:: በቦሩ ሥላሴ መርደ ተለቅሶላቸዋል:: የቦሩ ሥላሴ ሊቃውንት ፍትሐት ፈትተውላቸዋል:: መወድስ ዘርፈውላቸዋል:: አባታቸው ዐራት ዐይናው ተፈሪ ከጎጃም እስከ ጎንደር ከትግራይ እስከ ሸዋ በየቅኔ ቤቱ ተንከራትተው ተስፋ ቆርጠው መርደ አቁመው አልቅሰው ቀብረዋቸዋል:: መቃብራቸው ግን ይህ ስዉር ዓለም ነበር:: ገሞራው አሁንም ሰዎችን እንደሰው ለመቀበል እያመነታ ነበር:: በተለይ ጠቢቡ ሖረን ባያገኝ ኑሮ ምን ሊውጠው እንደሚችል ሲያስበው ጨነቀው:: ሖረ ወደ ዐራት ዐይናው ወስደው ማስተዋወቅ ጀመሩ::

"እኛ ሁለቱን ዓለማት ስንጠብቅ የተዋነይ ውኃ ጉድ ሠራችን:: ውኃውን ጠጥተው ስዉሩን ዓለም ደፈሩት:: ይቅር ይበሏቸው:: ቅኔ ቤት ሳሉ አውቃቸዋለሁ:: የቅኔ ተማሪዎች ናቸው:: መጽሐፍም ቀጽለዋል:: ከጎንጅ ቅኔ ቤት ነው





የመጡት:: እያ ፋሬስ ነው የላካቸው:: በሊቅነት እኛን ይመስላሉ::" አሉ ጠቢቡ ሖረ::

"እንኳን ደኅና መጣችሁ! ወደዚህ ዓለም እያሌ የቅኔ ተማሪዎች ይመጣሉ:: ገብተው ግን አያውቁም:: በመጡበት እግራቸው ተመልሰው ይሄዳሉ:: ከቅርብ ቀን ወዲህ ደከተሮች ጭምር ብቅ ብቅ ማለት ጀምረው ነበር:: ደቅ ገዳምን ተሳልመው በመጡበት እግራቸው ተመልሰው ሂደዋል:: ወደ ስዉሩ ዓለም እንዳይገቡ ተሰውሯቸዋል:: እኛም በሰዋሬ ሆነን የድንጋይ ናዳ እያወርደን አስደንብረናቸዋል:: ወሬ ሰምተው በየቅኔ ቤቱ የመጡ ተማሪዎች "እግሬ አውጭኝ" እያሉ ፈርጥጠዋል:: የእናንተ አመጣጥ ግን እውነተኛ አመጣጥ ይመስላል:: በድጋሜ እንኳን ደኅና መጣችሁ:: ከደርግ ዘመን ጀምሮ እስካሁኗ ሰዓት እንደናንተ በሰዋሬ ወደዚህ የመጣ ሰው ገጥሞኝ አያውቅም:: ለመሆኑ ይህንን የሰዋሬ ጥበብ ማን ሰጣችሁ?::" አሉ ቀለሙ ተፈሪ በግእዝ ቋንቋ::

"የቅኔ መምህራችን ሊቁ ፋሬስ ዘደብረ ጥበብ ናቸው:: ከተዋነይ ውኃ ከጠጣን በኋላ ይህንን ዓለም መርጠን:: ከደብዳቤ ጋር ወደዚህ ላኩን::" አለ ገሞራው::

“እናንተ ገና ጮርቃ ወጣቶች ናችሁ፡፡ እንዴት ሊሰጧችሁ ቻሉ?” አሉ ዐራት ዐይናው፡፡

“መርጠነው ነው፡፡ ደብዳቤ ጭምር ይዘናል፡፡ አድርሱ የተባለው ደግሞ ለእርስዎ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ዐራት ዐይናው የሚል አድራሻ ተጥፎበታል፡፡ ፎቶ ግራፍ ጭምር አለው፡፡ ይኸው ደብዳቤውና ፎቶው፡፡ የወጣትነት ፎቶዎ ይመስለኛል፡፡” ብለው ፎቶውንና ደብዳቤውን ሰጧቸው፡፡

ዐራት ዐይናው ከተዋነይ ሀገር ወደስዉሩ ዓለም የተላከውን ደብዳቤ ገልጠው ማንበብ ጀመሩ፡፡

“ዐራት ዐይናው ሆይ! እንደምን አለህ? ለጤናህ ምናምን እንዳልልህ ባንተ ዓለም ጤና ማጣት የለም፡፡ ጤናችሁ ከተፈጥሮ ጋር ተስማሚ ነው፡፡ በዚህ በእኛው ከተማ ግን የጤናችን ነገር አሳሳቢ ሁኗል፡፡ ሕዝበ አዳሜ መድኃኒት ለመግዛት ሰልፍ ላይ ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ ማስታገሻ እንጂ ፍቱን መድኃኒት እምብዛም ነው፡፡ ሕዝብ እያለቀ ነው፡፡ ዘመኑ የመሞት ዘመን ሳይሆን የመጠረግ ዘመን ስለሆነ አሮጌው ትውልድ በመጥረጊያ እየተጠረገ ይመስላል፡፡ አሁን ያ ነገር በእኔም መምጣቱ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ እምና ላይ የሞት ቀጠሮ አልነበረኝም፡፡ ዘንድሮ ግን ፈርቻለሁ፡፡ ከቅርብ ቀን ወዲህ ደግሞ ሕልሜ በራሱ አስፈርቶኛል፡፡ ድሮ በሕልም አላምንም ነበር፡፡ ከቅርብ ቀን ወዲህ ግን እንደ ዮሴፍ በሕልም ማመን ጀምሬአለሁ፡፡ አለማመን ይሻለኝ ነበር፡፡ ከመንሁ ወዲህ በሕልሜ ስመነኩስ አድራለሁ፡፡ መንኰሰ ማለት ምን ማለት ነው? ‘መንኰሰ በላ’ ብለህ በዘመናዊው ግስ እንደማትፈታው አምናለሁ፡፡ መንኰሰ ማለት ቀጥተኛ ፍቺው ‘ሞተ’ ማለት ነው፡፡ መነኩሴ ማለትም ምዉት ማለት ነው፡፡ አበቃ! ይህንን የመሰለ ትርጉም ያለው ሕልም አይቼ መልአከ ሞትን ብፈራ አትፍረድብኝ፡፡ በእርግጥ ፍርሐቴ የሞትን ጽዋ አይደለም፡፡ ያንን የንብስተ መናውን ጥበብ ለቀለም ልጆቼ ባለማውረሴ ነው፡፡ ደብዳቤው ከእጅህ እንደገባ እንዳትውል እንዳታድር፡፡ ያንን የመናውን ጥበብ ምሥጢር ገልጠህ አስተምራቸው፡፡ ከዚህ ከተዋነይ ደሴት ውስጥ የሰዋሬው መጽሐፍ አለ፡፡ ነገር ግን የመናው ጥበብ ተገንጥሏል፡፡ ሁለቱ ከተነጣጠሉ ደግሞ ዋጋ የለውም፡፡ በስዋሬ መኖር መልካም ነበር፡፡ ነገር ግን በስዋሬ ሲኖሩ ረሐብ አለ፡፡ ችግር ደግሞ ክፉ ነው፡፡ ሰው የፈለገውን ያኽል ተሰውሮ ቢኖር ሰው ስለሆነ ይራባል፡፡ ይጠማል፡፡ የሆድ ነገር ጭንቅ ነው፡፡ ያ የረሐብ መድኃኒት ደግሞ በእናንተ በጠቢባኑ መዳፍ ነው፡፡ በስዉሩ ዓለም ያሉ ሴቶች ያውቁታል፡፡ ይህ እኩይ ዘመን እስኪያልፍ በእናንተ በጠቢባን ዓለም ይቆዩ፡፡ ይህ ክፉ ቀን እስኪያልፍ በመናው ምሥጢር ይጠቀሙ፡፡ ያ

የተዋነይ ውኃ..." መግለጥ አትቷቸው እንጂ በረጅሙ መተንፈስ ፈልገው ነበር-ተሰሙ ተፈራ::

"ወቺው ጉድ! ደግሞ ምን ተፈጠረ?" አሉ ደቀኛው::

"ምን ያልተፈጠረ ነገር አለ! ይኸውና በዛሬው ዕለት እኔና ወንድሜ ሖረ ከስዉሩ ዓለም በር ላይ ቁጭ እንዳልን ሁለት የቅኔ ተማሪዎች የተዋነይ ውኃ ቀምሰው አጥሩን ጥሰው ስዋሬውን በጥሰው ዘው ብለው ሲገቡ ዐይን ለዐይን ተገጣጠምን:: እኛ ባናግዳቸው ኑሮ ከዚህ ድረስ ሰተት ብለው ሊገቡ ምንም አልቀራቸውም ነበር::" ሲሉ ጠቢባኑ በድንጋጤ ክው አሉ:: ዐራት ዐይናው ፋታ ወስደው አከሉበት::

"በእውነት ተደፍረናል! የቅኔ ተማሪዎች ደፍረውናል:: ድሮም የቅኔ ተማሪ ሰይጣን ነው ይባል ነበር:: ሐሰት የለውም:: በተዋነይ ውኃ መክስትነት ስዉሩ ዓለም ተበረበረ::" አሁንም በጽሙና እያሰቡ ቀጠሉ::

"ከስዉሩ ዓለም ድረስ ሰተት ብለው የገቡት የጎንጅ ደብረ ጥበብ የቅኔ ዘራፊዎች ናቸው:: ጠቢቡ ሖረ በመልክ ያውቃቸዋል:: አመጣጣቸውንም ደርሶበታል:: ከተዋነይ ውኃ በኮዳ ይዘዋል:: ከስዉሩ ዓለም ለመኖር እንደመጡ ፍንጭ ሰጥተውናል:: ስዉሩን ዓለም በተዋነይ ውኃ ገርስሰውታል::





ደብዳቤ ጭምር ይዘዋል:: በደብዳቤው ውስጥ የእኔ ስም ተጠቅሷል:: ፎቶዬ ጭምር አለ:: እያ ፋሪስ እንደሳካቸው አውቄአለሁ:: አሁን የቀራቸው ነገር ቢኖር ከጠቢባኑ ደቂቀ ተዋነይ ጋር መቀላቀል ብቻ ነው:: ይህንን ጉባኤ በደወል የሰበሰብሁት አንድ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለማሳሰብ ነው::" ብለው ቁጭ ሲሉ ጠቢባኑ ዐይን ለዐይን ተጋጩ:: ደቀኛው ዐይናቸው በንዴት ቀላ:: ገዳማዊው ወይራው በወይራ በንጋቸው መሬቱን እየደቀደቁ ሲያኩተመትሙ ቆይተው

"ዐራት ዐይናው ሆይ! እየቃዡ መሰለኝ:: ቅዠት በዚህ በስዉሩ ዓለም እንደሌለ ባውቅም አሁን ግን እየቃዡ ይመስለኛል:: ነፍስዎ መኻል ሀገር ሂዳ ማደር የጀመረች ቀን ቅዠት ይጀምርዎታል ብዬዎት ነበር:: ንግሬ ደርሶ ይሆን? "ሁ..ሁ..ሁ..." ይህንን የጠቢባን ዓለም ለማግኘት እልፎች ዳክረዋል:: ጠቢባን ባዝነዋል:: የአውሬ ሲሳይ የሆኑትን ደግሞ ጫካው ይቁጠራቸው:: በሽፍቶች የተቀጠፉትን ቀስቱ ይቁጠራቸው:: ያም ሆኖ ስንትና ስንት ጠቢባን ደክመው ደክመው ሲያቅታቸው የተሠወረ ዓለም የለም ብለው ዘግተዋል:: ከስንት ፈላስፎች ዐይን ተሰውሮ የቀረ ዓለም እንደሆነ እርስዎ ያውቃሉ:: ጃንሆይ ሳይቀር የቤተ መንግሥቱን ጠቢባን ወደዚህ ዓለም ልከው ሊደርሱበት ያልቻሉት የጥበብ ዓለም ነው:: በዚህ ዘመን የትኛው ጠቢብ

ነው ገልብጦት የገባው? እስኪ ይንገሩን? ስጧር ዓለም ጥሰ የሚገባ የቆሎ ተማሪ ተፈጠረ የምትሉት ነገር እውነት አይመስልም፡፡" ብለው ቁጭ ሲሉ ዐራት ዐይናው ሲያብረቀረቁ ከመቀመጫቸው ብድግ ሲሉ ደቀኛው ቀድመው ተነሡ፡፡ በንዴት እንደጦፉ ገጻቸው ይናገራል፡፡ ዐይናቸው እንደሰካራም ዐይን ቀልቷል፡፡ ጭቅጭቅ በርበሬ በመምሰሉ የገሞራውን ዐይን ተካክሷል፡፡

ብድግ እንዳሉ ቀጠሉ ደቀኛው፡፡

"እኔ ከርታተው ወደመኻል ሀገር ዘወር ዘወር ባልሁባቸው ቅርብ ጊዜያት የጥበብ ሰዎች መኻል ሀገር እንደሌሉ ተረድቻለሁ፡፡ ሊቁም መናፍቁም አዲሳባን ተቀላቅለዋል፡፡ በዚህ ዘመን አዲሳባ የገባ ሊቅ ደግሞ በሊቅነቱ መቀጠሉ ያጠራጥራል፡፡ መንፈቅ ሳይኖር ገሚሱ በድሎት ከፊሉ በችግር ነፍስ ይመታል፡፡ ከሊቅነት ወደተራ ሕዝብነት ይሸጋሸጋል፡፡ ከዓመት በኋላ ተራ ሕዝብ ሆኖ ቁጭ ይላል፡፡ ይህ በራሴ ጭምር ደርሶብኝ ነበር፡፡ ጥበቡ ቀርቶ የቅኔ ዜማ ልክ ይጠፋል፡፡ ማንኛውንም ሊቅ እንጀራ ቢቀናው ድሎቱ ያዘናጋዋል፡፡ ችግር ሲቀፈድደው ለቁራሽ ሲል ሊቅነቱን ረስቶ የሀብታም ኪስ ሲያመልክ ይኖራል፡፡ እኔ አዲሳባን እርግፍ አድርጌ የተውሁት ለዚህ ነበር፡፡ ሊቅነቴን ሲሸረሽረው





የቀደመ ሰብእናዬን ሲጋፋኝ አእምሮዬ ማሰብ አቁሞ ጨንራዬ አኽል መፍጨት ጀመረ፡፡ በደጎናው ቀን ትቸው ወጣሁ፡፡ ከአዲሳባ ወጥቼ ቀጥታ ጎንደር ገባሁ፡፡ ጎንደር ውስጥ ቁጭ ብዬ ለወራት በተመስጦ ሰጥሜ ሳሰላስል ሰነበትሁ፡፡ ሕይወትን ፍለጋ ላይ ነበርሁ፡፡ የቅኔ ቤት ደስታዬ ወዴት አለሽ? እያልሁ፡፡ ባንድ ደግ ቀን ወደቀደመ ሰብእናዬ ስመለስ ታወቀኝ፡፡ ስድስተኛው የስሜት ሕዋሴ የነገረኝ ይመስለኛል፡፡ በዚች ምሽት አበቅ የለሽ ጠጅ ቤት ጎራ አልሁ፡፡ ጠጅ ቤቱ በሊቆች ደምቋል፡፡ አዲስ አበባና ጎንደርን ለማነጻጸር ይረዳኝ ዘንድ አበቅየለሽ ጠጅ ቤት ቁጭ ብዬ መርካቶን አሰብኋት፡፡ አዲሳባ ሳለሁ መርካቶ ጠላ ቤት ጎራ ብዬ አፍለኛውን እቀጥፍ ነበር፡፡ ነገር ግን በአበቅየለሽና በመርካቶ ጠላ ቤት ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ አበቅየለሽ ከጠጁ ጎን ለጎን በሊቆች አንደበት ወረብ ይንቆረቆራል፡፡ ማኅሌተ ገንቦ ይወርዳል፡፡ ሥጋዬ ከጠጁ ነፍሴ ከወረቡ ጨልጣ ቤቴ ተመለስሁ፡፡ መርካቶ አንቡላ እንጂ ንጹሕ ጠላ ወዴት ተገኝቶ? ለስሙ ጠላ ቤት ቢኖርም አንቡላ ቤት ነበር፡፡ ከጠላው በመለስ የወንበዴዎች ዱላ ይቀጥላል፡፡ ሰካራሞች በጠላ መዓዛ ብቻ ይሰክራሉ፡፡ እንግዲህ አዲሳባ የገባ ሊቅ እኔን ሊመስል ይችላል፡፡ እኔን ባይመስል እንኳ ከአዲሳባ ሊቅ አንዱን መስሎ የመኖር ግዴታ አለበት፡፡ ገጠር ሳለ የነበረው ሊቅነት

አረታዊት ድንጋይ ማለት ነው፡፡ እስራኤል ውኃ ሲጠማቸው ሙሴ ውኃ! ሙሴ ውኃ! እያሉ ይጮኻሉ፡፡ በድጉ ከያዛት ድንጋይ ውኃ አፍልቆ ያጠጣቸዋል፡፡ ሲርባቸው ሙሴ መና! ሙሴ መና! እያሉ ይጮኻሉ፡፡ መና ከደመና አውርዶ ይመግባቸዋል፡፡ ቤተ እስራኤል የፊንቆንን አፈር ሲረግጡ ግን መና መዝነብ ቆመ፡፡ ያችን የሙሴ ድንጋይ ቢፈልጉ አጧት፡፡ ከመዳፋቸው ላይ የቀረውን መና በመሶበ ወርቅ አድርገው ከቤተ መቅደስ አግብተው አኖሩት፡፡ መና መውረዱ ግን እንደጥንቱ ሊቀጥል አልቻለም፡፡ እያረሱ እየቆፈሩ በላባቸው መመገብ ጀመሩ፡፡ ከቤተ መቅደስ በመሶበ ወርቅ ያኖሩት መናም ጌታ ሰው ሲሆን የደረሰበት አልታወቀም፡፡ ቤተ እስራኤል አሁንም የዚህ ጸጸት አለባቸውም፡፡ አባቶቻቸው መና ከደመና የተመገቡበትን ተአምር፣ ጥበብ ነው ብለው ወስነዋል፡፡ ይኸውም ሲታወቅ ሙሴ ያችን ድንጋይ ወዴት እንደወረወራት መመርምር ጀምረዋል፡፡ ነገር ግን አሁን ድረስ ምንም ፍንጭ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ ምን አልባት ከታቦተ ጽዮን ጋር ወደኢትዮጵያ ገብታ ሊሆን ይችላል በሚል እሳቤ ኢትዮጵያን እየበረቀሱ ይገኛሉ፡፡ የይሁዲ ፈላሻዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የማይጠፉት በትክክል ጽዮንን ፈልገው አይደለም፡፡ ተአምረኛዋን የሙሴን ድንጋይ ኀሠሣ ነው፡፡" ብለው ከተረኩ በኋላ





"አሁን ግን ስለ ሙሴ ድንጋይ የሚገልጽ የታሪክ መዝገብ በመኻል ሀገር እንደሌለ እናውቃለን፡፡ ያን ታሪክ የሚዘክሩ መጻሕፍት ያሉት በዚህ በስዉሩ ዓለም ውስጥ ብቻ ነው፡፡ በመኻል ሀገር ስለዚህ ጉዳይ የሚጠቁም የታሪክ ሽርፍራፊ እንደሌለ እናውቃለን፡፡ እኒህ የቅኔ ተማሪዎች ወደ ስዉሩ ዓለም የመጡት ምን መረጃ ይዘው ነው? ይህንን ጠይቃችኋል?" አሉ ደቀኛው፡፡

በመኻል ጠቢቡ ሖረ ብድግ ብለው ቀጠሉ፡፡

"መጠየቅስ አልጠየቅንም፡፡ ነገር ግን እኒህ የቅኔ ተማሪዎች ተራ ጀቢራ ተማሪዎች አይደሉም፡፡ ከተዋነይ ቅኔ ቤት ቁጭ ብለው የሀገር ታሪክ ሲያጠኑ በዐይኔ አይቻለሁ፡፡ በዚያ ላይ የታሪክ መዛግብትን በትክክል ሲፈትሹ የኖሩ ናቸው፡፡ ከቅርብ ቀን ወዲህ ደግሞ ያ አያ ፋሬስ አልፎ አልፎ የሚዘርፋቸው ቅኔዎች አነጋገሪ ሆነዋል አሉ፡፡ ስለ መናውም ቅኔ ዘርፏል ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ ያንን አጥንተው የመጡ ይመስለኛል?፡፡" አሉ ጠቢቡ ሖረ ለጠቢባኑ ሲመልሱ፡፡

"እልፍ አእላፍ መወድስ ቢዘርፍ ስለኀብስተ መናው መወድስ እንዳማይዘርፍ አምናለሁ፡፡" አሉ ደቀኛው፡፡



Scanned with CamScanner

"መወድስማ ዘርፏል። ያን መወድስ ተከትሉ እልፍ የቅኔ ተማሪዎች ወደስዉሩ ዓለም መጥተው ከመናው መቋደስ እንደሚፈልጉ እኔ መኻል ሀገር ሳለሁ ደርሼበታለሁ። እንዲያውም መወድሱን ራሴ ሰምቼው ነበር።" ሖረ መወድሱ እንደ ተዘረፈ ምሥጢር እንደ ወጣ እንቅጯ አድርገው ተናገሩ።

"መጠርጠሩማ አይከፋም።" አሉ ጠቢቡ ሖረ አሁንም።

እንደሚታወቀው በመኻለኛው ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የውጭ ሊቃውንት ኢትዮጵያን አሥሠዋታል። ጽንፍ እስከጽንፍ አድርሰዋታል። ከዛጉዌ ዘመነ-መንግሥት እስከ መካከለኛው ዘመን ድረስ ኢትዮጵያ በውጪ አሣሾች ታርሳለች። እስከ አሁን ግን ስለመናው ምሥጢር ያየ የሰማ ፍጡር አልነበረም። አሁን አሁን ግን የቅኔ መዛግብትን የሚፈትሹ የግእዝ ቋንቋ ሊቃውንት በርክተዋል። እኒህም ድርሳናት ከሚገነጽሉ ሊቆች ይመደባሉ። ስለመናው ምሥጢር ሊያውቁ ይችላሉ። ጌታ "አበዊክሙሰ መና በሉ በገዳም" ብሎ አስተምሯል። ጌታ ያስተማረውን ይዘው ይህንን መና ለመፈለግም የሚዳክሩ አያሌ ሊቆችን አውቃለሁ። እኒህስ የጌታ ቃል ሰቧቸው መጥተውስ ቢሆን? "አባቶቻችሁ መና በሉ" ብሎ ጌታ ያስተማረውን ቃል መነሻ





አድርገው መናው ምድራዊ መና መስሏቸው መጥተውስ ቢሆን?።" አሉ ጠቢቡ ሖረ አሁንም ወደሌላ ምሥጢር ተራምደው።

ጓሬ ተው ሖረ! በዚህ ዘመን ያንን ያኽል ሊቅ ሊኖር? አይመስለኝም! በእውነት አይመስለኝም! ከእኛ በፊት ይህ አምላካዊ ቃል ከስብከቱ በስተጀርባ ምድራዊ ምሥጢር ሊኖረው ይችላል ብሎ የሚገምት ሊቅ አልነበረም።

እኛ ግን መጽሐፉን ጎንደር ስንቀጽል አንሥተነው ነበር። መምህራችን ዘለፉን። መናፍቅ ከምንባል ብለን ሰማያዊውን ተምረን መና ከደመና የሚወርድበትን ፍልስፍና ሳንጠይቅ አለፍነው። በእኛ ጊዜ የመናውን ምሥጢር በጉባኤ ማንሣት ነገረ መለኮትን እንደመጣስ ይቆጠር ነበር።" አሉ ደቀኛው።

"ያሁኑ ተማሪ ግን ይህንን የመሰለ ምሥጢር ከመጠየቅ ወደኋላ አይልም። በተለይ ገሞራው ይህንን ለመሰለ ምሥጢር ቅርብ ነው ሲባል ሰምቻለሁ። ከምሥጢሩ ጎን ለጎን ፍልስፍናውን ጭምር ካላጠና ደስ አይለውም። በእኔ ግምት መናው ከዚህ ውስጥ መኖሩን የደረሰበት ይመስለኛል። አመጣጣቸው ለዚህ ይመስለኛል።" አሉ ጠቢቡ ሖረ።



Scanned with CamScanner

"እርግጥ ነው! ወንጌላዊ ዮሐንስ ስለመናው ምሥጢር አሳምሮ እንደጻፈ እናውቃለን። ይህን ተከትሎ የኢትዮጵያ ሊቃውንት መልእክ ሞትን የሚገዝት ኅብስተ መና ሲያሥጨ ኦረዋል። ይህ ስፍራ ግን የተገለጠላቸው በጣት ለሚቆጠሩት ብቻ ነበር። እነሱም ቢሆን ምሥጢሩንና ስፍራውን ደብቀውት ኖሩ እንጂ ለመጣው ሁሉ የጥበብ ቤታቸው ክፍት አልነበረም። እኛም የእነሱን ዐሠር ተከትለን ከርችመነው ኦረናል። አሁንም ያ መንፈስ መቀጠል አለበት። ዛሬ ከመሬት ተንሥተን ስፍራውን ለማንም የቅኔ ተማሪ መፈንጫ አናደርገውም። እኒህ የቅኔ ተማሪዎች ወደውስጥ መግባት የለባቸውም። ወደመኻል ሀገር ይመለሱ።" አሉ ደቀኛው።

"ምንም የቀራቸው ምሥጢርኮ የለም። ከጠቢባኑ ከመቀላቀል በቀር ሁሉንም ቃኝተውታል። አሁንም ከኪዳነ ምሕረት ጠበል ቤት ከዋሻው ናቸው። ከዚያ ዘግተንባቸው ነው የመጣነው። ነገር ግን ስዋሬውን ገርስሰው እኛን ለማየት ችለዋል። እንደማነኛውም ተራ ሕዝብ ለሱባኤ የመጡ ሕዝባዊ አይደሉም። ተዋነያዊ ናቸው።" ካሉ በኋላ "ወደመኻል ሀገር ተመልሰው ቢሄዱ የበለጠ ምሥጢር ሊያወጡ ይችላሉ። እንደእኔ እሳቤ ከሆነ በክብር እንቀበላቸውና እኛን ይምሰሉ።" አሉ ዐራት ዐይናው።





"ይቺ ናትና! ይግቡ! ይቀላቀሉ! ወይኔ ደቀኛው! ወይኔ ሞገደኛው! በዚህ ዘመን ወደ ስውሩ ዓለም የማንም የቆሎ ተማሪ ሊገባ? ከመግባታቸው በፊት እኔ ወደ መኻል ሀገር ሄጄ የሞት ጽዋዬን እጠጣለሁ! እኔ ከስዉሩ ዓለም እያለሁ ግን ይህ ስሕተት አይሠራም።" ጉባኤውን ረግጠው ሊሄዱ ሲነሡ ወይራው ጨምድደው ይዘው ባጭሩ ተናገሩ። እስካሁን ውዝግቡን እየሰሙ ሲገረሙ ቆይተው ነበር።

"እኒህ የቅኔ ተማሪዎች በእድሜ ልጆች ከሆኑ ይህ ስዉር ዓለም ሊያንጓቸው አይችልም። ከመናው በቀር ስዉሩን ዓለም፣ ዓለማችን ብለው ሊመርጡት አይችሉም። ወደውስጥ ቢገቡ ከመናው ቀምሰው ወደመኻል ሀገር ይመለሳሉ። እናም ወደ ውስጥ መግባትና ከመናው መቋደስ የለባቸውም።" አሉ ወይራው ጠበቅ አድርገው። ጠቢባኑ ነገሩን በነጋታው ለማንሣት ተስማምተው ዐራት ዐይናው ፈጠን ብለው በጸሎት ዐሥረው ጉባኤው ያለአንዳች ስምምነት ተበተነ። ዐራት ዐይናው ወደ እነገሞራው ተመለሱ። አመጣጣቸውን ሊያናዝዟቸው በአእምሯቸው ጥያቄ እያሰላሰሉ ለአራት የሚሆን ከደቅማው ዛፍ ፍሬ ታቅፈው ሲመለሱ ሌሊቱ ኩልል ብሎ ነበር።

“ጫፍ ድረስ ንገረኝ ካላችሁ በአስማት ጃንሆይን ከፈተናቸው መነሣት እችላለሁ፡፡” አሉ

“ደስ ይለናል፡፡” አለ ታሪኩ፡፡

“ብጃንሆይ ዘመን አባተ የሚባል አስማተኛ ነበር፡፡ ሲፈርድበት በዕፅ እሰወራለሁ፤ ሀገር አፈርሳለሁ እያለ አስወራ፡፡ ወሬ ብቻ አይደለም፡፡ ተፈላስፎም አሳይቶ ነበር፡፡ አስማተኛው የቤተ-መንግሥት ሰዎችን በመፈታተን ይታወቃል፡፡ ሽቅብ ወጥቶ በጌቶች ዙፋን ላይ ካልሸናሁ የሚል ጉደኛ ነበር፡፡ የጥበብ ስሙ አባተ ነው፡፡ የቤተ ክህነት ሰዎች ግን አብ-አንተ ሲሉ ይጠሩታል፡፡ “የምድር እግዜር አንተ ነህ” እንደ ማለት ነው፡፡ በስዉር ከኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት እየገባ ከጃንሆይ ጋር ማዕድ እንደሚጋራ ተደረሰበት፡፡ ወሬው ከጃንሆይ ንቁ ጆሮ ደረሰ፡፡ ጃንሆይ ቤተ መግሥታቸው መደፈሩ ቈጭቷቸው አባተን ይዘው ለማሠር ፈለጉ፡፡ አስማተኛው ግን በአስማቱ እየተጠቀመ ሊጨበጣቸው አልቻልም፡፡” “ቂቂቂቂ” ብለው ሲስቁ ሁለቱም በፈገግታ አጀቧቸው፡፡ ሦስቱም የሊቅ ሳቅ ሳቁ፡፡ የሊቅ ሳቅ ቀጭን ናት፡፡ ስቀው እንዳበቁ

“እረ በማርያም! ያን ያኽል ምን አስማት ቢጨብጥ ነው፡፡” አለ ገሞራው፡፡





“እረ እንጃ አባቱ ልጄ! የሚጠቀመው ግን አፈር ብቻ ነበር፡፡” አሉ እንደ ዋዛ፡፡ ቀለሙ ተፈሪ ንግግራቸው እንደ ዋዛ ናት፡፡ የከረረ ጉንጭ አልፋ ንግግር አይወዱም፡፡

“የምን አፈር?”

“የምን አፈር ልበልህ! አታጋልጠኝኮ ነው ማለት!” ቂቂቂ ብለው የዕለቱን ቀጭን ሳቅ ሲስቁ ቆይተው በከፊል ማብራራት ቀጠሉ፡፡

“ጉደኛው አባተ ፊት የቅኔ ቤት ጓዴ ነበር፡፡ ቅኔውን እንደፈጸመ የአዲሳባ ነዋሪ ሆነ፡፡ ከዚያም ከዚያም መነታትሮ በከተማው ውስጥ የወፍ ጎጆ ቢጤ የምታክል ባሕላዊ ጎጆ ቀለሰ፡፡ ከጎጆዋ ራቅ ብሎ ደግሞ የተንጣለለ ሣር ቤት ሠራ፡፡ ሁለቱም መኖሪያ ቤቶቹ ባሕላዊ ቤቶች ነበሩ፡፡ በሁለቱ ቤቶቹ ውስጥ የተለያዩ መደቦችን ደረደረ፡፡ እነኚህ መደቦች ከጭቃ የተሠሩ ሲሆኑ የመደቡ አፈር ከተለያዩ ሀገራት የተሰበሰበ አፈር ነበር፡፡ ያንን አቡክቶ መኖሪያ ቤቱ ውስጥ ወደሰባት ያኽል መደቦች ሠርቷል፡፡ ከቤቱ ውስጥ ከሐረር ከአስመራ ከጅጅጋ ባሕርዳር ከጎንደርና ከተለያዩ ከተሞች በመጣ አፈር የተሠሩ መደቦች ከዚህ ከዚያም ተደርድረዋል፡፡ ከእሱ በቀር መደቦቹ ላይ የሚወጣ ሰው አልነበረም፡፡ መደቦችን በእግር መርገጥ ጭምር ክልክል ነበር፡፡ የጭቃ መደቦቹን ሠርቶ

እንደ ጨረሰ አስማት አከለበት:: ከጃንሆይ ጋር በተጣላ ሰሞን መደቦችን ለሥራ አዋላቸው::" ሲሉ ገሞራውና ታሪኩ በግርምት ተመለከቷቸው:: ከዚያም አከሉበት::

"ከጃንሆይ ጋር ፊት በተሿሿሩ ሰሞን ለመሰወር ሲፈልግ ሰኞ ከጅጅጋ አፈር ላይ ቆጭ ይላል:: ዛሬ አባተ ጅጅጋ ገባ ተብሎ ኀሠሣው ጅጅጋ ይጀመራል:: የሱማሌዋ ከተማው ውጥንቅጧ ይወጣል:: ቅራቅንቦዋ ይበረበራል:: ጓዳዋ ጉድጓዳዋ ይመነቀራል:: ሽለቆዎቿ ይታመሳሉ:: በነጋታው ደግሞ ከአሥመራ ካመጣው አፈር ላይ ቆጭ ይላል:: አባተ ወደአሥመራ ኮበለለ ተብሎ አሥመራ ላይ ይታደን ይወጣበታል:: ረቡዕ ከሐረር ካስመጣው አፈር ላይ ቆጭ ይላል:: አሁንም ዘመቻው ሐረር ላይ ይጦጧፋል:: ቤቱ ቁጭ ብሎ በጃንሆይ ላይ ምትሐት እየሠራ እንደልቡ ይኖር ነበር:: በኋላ ይህ ምሥጢር ተመረምሮ ተደረሰበት:: አንድ ቀን ወገቡን ሲፈትሽ ሽንት ቤት እንደገባ በቁጥጥር ሥር ዋለ:: ጃንሆይ ከኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት አስገብተው ዐሠሩት:: ከዚያም ምግብ እንዳይገባለት ከለከሉ:: አባተ እንደታሠረ ረሐብ ፀናበት:: ወደማታ ሲርበው ሰይጣኑን በአስማት ስቦ መብል መጠጥ እንዲያመጣለት አዘዘው:: ያም ሰይጣን ከኢዮቤልዩ ቤተ-መንግሥት ገብቶ ራሳቸው ጃንሆይ ከሚመገቡት ምርጥ ምርጡን መብል መራረጠ::





ሙዳ ሥጋ:: የመተሐራ ፍራፍሬ:: ሞንዳላ ነጭ ጤፍ እንጀራ:: ከሚጠጣውም ጨማምሮበታል:: ጠጅና ወይን ጭምር ተዳብለዋል:: ሰይጣኑ ከጃንሆይ ገበታ መብል መጠጥ ይዞ አባተ ወደታሰረበት ክፍል ዘለቀ:: አባተ ከውስጥ ሰይጣኑ ከበር ቆሞ በቃል ሰብአዊ ሲነጋገሩ ጃንሆይ ሉሉ የተባለውን ውሾቻቸውን ከፊት ከፊት አስቀድመው ብቅ አሉ:: አባተና ሰይጣን ወሬአቸውን ገቱ:: ጉደኛው ሉሉ ከፊት ወደኋላ ከኋላ ወደፊት እየተውተረተረ ጮኸቱን አቀለጠው:: ጃንሆይ ሉሉ ወደሚጮኽበት በኩል ሲሄዱ ምንም ድምፅ የለም:: ኮቴም የለም:: ድምፀ ሰብእ በሌለበት ባዶ ሜዳ ላይ ሉሉ ብቻውን ይንተገተጋል:: መላው ሲጠፋባቸው ተመልሰው ገብተው ተኙ:: ያ ሰይጣንም ከበሩ ተገትሮ አደረ:: እንዳይሄድ አባተ በአስማት አውግዞታል:: ወደ ውስጥ እንዳይገባ ቤቱ ተከርችሞበታል:: ጉዱ የፈጠጠው ከዚህ ላይ ነበር::" ብለው እንባ በደረታቸው እስኪወርድ ይስቁ ጀመር::

"ሰይጣንኮ ረቂቅ ነው ይባላል:: ለምን አልገባም:: እንዴት በር ይዞ ሊያቆመው ቻለ? ይህ እውነት አይመስልም:: ልክስክሱ ሰይጣን ካልሆነ በቀር በር ሊገታው የሚችል ተፈጥሮ ያለው አይመስለኝም::" አለ ታሪኩ



Scanned with CamScanner

"ጉዱስ ከእሱ ላይ አይደል እንዴ? ሰይጣን ሬቲቅንቱን ተጠቅሞ ቢገባ መብልና መጠጡ ግዙፍ ነው::

ግዙፉን እንጀራ ደግሞ በተዘጋ በር ይዞ መግባት አልቻለም:: እንዳልኸው ሰይጣን ረቂቅ ስለሆነ የተዘጋ በር አያቆመውም ነበር:: እንጀራው ግን ግዙፍ ነው:: በበር ካልገባ ምንም ማድረግ አይቻልም:: ለሰይጣኑም ያቃተው ይህ ነበር:: ከብሔራዊ ቤተ መንግሥት ገብቶ በበር እንጀራ ተሸክሞ ቢወጣም በተዘጋ በር ገብቶ ለወዳጁ መስጠት ግን አልቻለም:: በዚህ ምክንያት ሌሊቱን በር ላይ ቁሞ አደረ:: ማለዳ ጃንሆይ ከቡር ዘበኛቻቸውን አስከትለው ቢሄዱ እንጀራው በእስር ቤቱ በር ላይ ተንልቶ ተገኘ:: ሰይጣኑ ከፊታቸው ተሰወረ:: ለእራት ከተመገቡት ከፊሉ የመተሐራ ፍራፍሬ አባተ ከታሠረበት ክፍል ከበሩ ቁጭ ብሎ ተገኘ:: ሰይጣኑ ግን ከፊታቸው ውልብ ብሎ ተሰወረ:: ጃንሆይ የምር የደነገጡ ያን ቀን ብቻ ነው ይባላል:: ከዚያ በፊት ቢደነግጡም ድንጋጤአቸውን ሰው ልብ ብሎት አያውቅም ነበር::" አሉ ዐራት ዐይናው የጃንሆይን ድንጋጤ በአእምሯቸው እየሳሉ::

"ከዚህ ክስተት በኋላ ምን እርምጃ ወሰዱ?" ገሞራው አሻቦ ቢጤ ድዱን እያሰጣ ጠየቃቸው::





"ጉረ ጉድ ነው! መዘዙ ቅኔ ቤት ድረስ ሰተት ብሎ መጣ እንጂ:: ይቺን የሚሠሯት የተዋነይ ደቀመዛሙርት ናቸው ብለው ከጎንጅ የቅኔ ተማሪዎች ከፊሎችን በቁጥጥር ሥር አዋሉን:: ያን ጊዜ እኔ ጎንጅ ደብረ ጥበብ ቅኔ ቤት ነበር:: በእድሜም የመጨረሻው ትንሽ እኔ ነበርሁ:: የጎጃሙ ገዢ ፀሐዩ እንቁ ሥላሴ ወታደር ልከው በበጌምድር በኩል አድርገው ወደሸዋ ወሰዱን:: በደብረ ማርቆስ በኩል ከሆነ ግርግር ሲነሣ ይችላል ብለው በበጌምድር በኩል አሾልከው ከጃንሆይ አደረሱን:: ብሔራዊ ቤተ መንግሥት ስንደርስ ጃንሆይ እሳተ ነበልባል ሆነው ተቀበሉን::" ብለው በትዝታ ወደኋላ ተመልሰው መተረኩን ቀጠሉ::

"አስማቱን የሠራው አባተ ነው:: የእናንተን መታሠር ምን አምጡ ነው? በሀገር የላችሁ!" አለ ገሞራው::

"እንግዲህ በአፈ ታሪክ ተዋነይ በስዉር ከዐጤ በካፋ ቤተ-መንግሥት እየገባ ማዕድ ይጋራ ነበር ይባላል:: በካፋም ተቸግረው እንደነበር ዜና መዋዕላቸው ይተርካል:: ጃንሆይ ከዘመናዊ እውቀት ጎን ለጎን ዜና መዋዕል አንባቢ ጭምር ነበሩ:: ዜና መዋዕል ሲጠቅሱ ያደጉ ሰው ናቸው:: ማዕዳቸው ሲደፈር የዐጤ በካፋ ዜና መዋዕል ትዝ አላቸው:: ከተዋነይ ደቀ መዛሙርት በቀር ማዕዴን ሲደፍር የሚችል የለም ሲሉ

ተፈጥሮን ተጠበበበት። መከስትም መሰወርም ያለው ከውኃ ጠባይ ነው። ማንኛውም ውኃ በተፈጥሮው ብርሃን አለው። በብሩህነት ተነሥቶ መክስት ሠራ። ታያርያ የሚለውን የጥበብ መጽሐፉን ብርሃን በሚተፋ በውኃ ቀለም ጣፈው። እንዳያችሁት በታብር ተሰወረ። እናንተም ,ስዉሩን ዓለም በታብር ገርስሳችሁት ገባችሁ። እኔና ሖረ ከዚህ ላይ ባናግዳችሁ ኑሮ አሁን ከጠቢባኑ ደቂቀ ተዋነይ እግር ሥር ነበራችሁ። ይህ ጥበበ ተዋነይ ከአስማትም ሆነ ከምትሐት ልዩ ነው ያልሁት ለዚህ ነው። አሁን እናንተ በታብር ትሰወራላችሁ ትከሰታላችሁ። ነገር ግን ብቻውን መሰወር በቂ አይደለም። ያ ከሆነ ረሐብ ይገድላል። ለዚህ ኀብስተ መናው መኖር አለበት። በዚህ ስዉር ዓለም ያለው ያ ሞትን የሚገታው የሞት መድኃኒት የሌለው ሊቅ፣ ሊቅነቱ ይፈተናል። ውስጡም ባዶ ነው። በሰባራ ገል ይመሰላል።" ዛሬ ደግሞ መጥቶባቸዋል።

"ስዋሬና መክስት በሁለቱ መንገድ ነው ያልሁት ይኸው ነው። በአስማትና በተዋነይ ውኃ ብቻ። የሊቆች ጥበብ በተፈጥሮ ውኃ ሲሆን የድኩማኑ ደግሞ በአስማት ነው። የዚህን ዓለም ስዋሬ ግን ቅድመ ጃንሆይም ሆነ ድኅረ ጃንሆይ ከነበረው አስማት ጋር ማዛመድ የለባችሁም። የአስማት መዓቱ ብዙ ነው። በዚያ ላይ የአስማት ጠቢባን





አስማታቸው ከሸፎባቸዋል። የደቂቀ ተዋነይ ጥበብ ግን ሠምሯል። ጥበበ ተዋነይን ያዙ። ነፋስ አትከተሉ። አስማትና ነፋስ አንድ ናቸው። ሊጨበጡ አይችሉም" ብለው ቀና አሉ። ሊነጋጋ ሲል ወፎች ዘመሩ። ዝማሬውን በተመስጦ ጠጥተው

"በዘመኔ ግን ይህንን ታሪክ አውቃለሁ። የአባተን መደቦች በደማ ያፈረስኋቸው እኔ ራሴ ነኝ። አስማትን በማጋለጥም የድርሻዬን ተወጥቻለሁ።" ሁለቱ የቅኔ ተማሪዎች መደነቅ ጀመሩ። ዐራት ዐይናው አንገታቸውን ዘመም አድርገው አሙለቁባቸው። ገሞራው ዐይኖቹን ሰመመን ውስጥ ጥሎ ይሰመነመናል። ተፈጥሮው ነው። ቁጭ ሲል ጠልቆ ያስባል። ሲንቀሳቀስ የሰው ፊት ያነባል። ገጸሰብእ የሚባል መጽሐፍ ሊጽፍም ይዳዳዋል። ገጸሰብእ እያነበበ መኖሩን ቀጥሎበታል።

"እናንት ግን በተዋነይ ውኃ ስለተሰወራችሁ ደስ አይበላችሁ። ጉዱ ገና ነው። ስዋሬን ጥልቅ ጥበብ አድርጋችሁ ልትኮሩ አይገባችሁም። መልአከ ሞትን የሚገዝተው ምሥጢር ይቀራችኋል። ከዚያ ለመድረስ የደቂቀ ተዋነይ ፈቃድ ያስፍልጋል። እነሱ ፈቅደው የሞትን አፍ እስካልዘጋላችሁ ድረስ እንኳን ደስ አላችሁ ልላችሁ አልችልም። ስዋሬ ብቻ ጥበብ አይደልም። ከአባተ የተሻለ ጥበብ እንዳልጨበጣችሁ መረዳት አለባችሁ። የጥበብ



Scanned with CamScanner

ቁንጮው የመናው ቁራሽ ነው፡፡ መናው ከተፈቀደላችሁ በመልአክ ሞት ላይ ሥልጣን አላችሁ፡፡" ብለው ጥበብ መሰል ምትሐቱን አጣጥለው የመናውን ጥበብ በከፊል ነካ አድርገው ካብራሩ በኋላ ሌሊቱ ሲነጋጋ ከዋሻቸው ወጥተው ወደጠቢባኑ ተመለሱ፡፡ ወደ ዘግባው ሥር...፡፡

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)
Telegram Channel





## ፲፯

ከጠቢባን ዓለም

በስዉሩ ሰማይ ሥር ፀሐይ ፏ ማለት ጀምራለች፡፡ ደቅ አስጠፋ እንደ ጥንቷ ጎንደር ቁስቋም ታሸበርቃለች፡፡ የነታሪኩ መግባትና ከመናው መቋደስ ገና አልተቋጨም፡፡ ዛሬም ስብሰባ አለ፡፡ ጠቢባኑ ደቂቀ ተዋነይ ተሰብስበው ይወስናሉ፡፡ ዐራት ዐይናው ቀለሙ በማለዳው ትልቁን ደወል ሲደልቁት ጠቢባኑ ድጋሜ ተሰበሰቡ፡፡ ክርክሩ በነጋታውም ቀጥሎ ዋለ፡፡ ገምራውና ታሪኩ ወደ ስዉሩ ዓለም በደረሱ በነጋታው የነበረው ውዝግብ ከቀዳሚው ዕለት ውዝግብ ይባስ ሲከር ጠቢባኑ ደቂቀ-ተዋነይ ከሁለት ተሰነጠቁ፡፡ ከፊሉ ወደ ስዉሩ ዓለም ገብተው፣ ከመናው ተቋድሰው፣ መልአከ ሞትን ገዝተው፣ ስዋሬውን ወርሰው፣ ጠቢባን ሆነው በሕይወት ይኑሩ ሲሉ ደቀኛው ደማቸው ፈላ፡፡ ስሜታቸው ገነፈለ፡፡ የፈላ ደምና የገነፈለ ስሜት ተጎናጽፈው የሁለተኛውን ቀን ጉባኤ ሲጀምሩ ጠቢቡ ሎሬና ዐራት ዐይናው ቀለሙ ተፈሪ ወደውስጥ ገብተው ከእኛ ጋር ይኑሩ፤ ከመናውም ይቋደሱ ሲሉ ጠበቃ ቆሙላቸው፡፡ ወይራውና ደቀኛው አጥብቀው ተቃወሙ፡፡



Scanned with CamScanner

ደቀኛው በስዉሩ ዓለም ውስጥ የመናው ኀላፊ ሲሆኑ የመናው በረከት በእጃቸው ነው። አልፎ አልፎም ወደ መኻል ሀገር ብቅ እያሉ መኻሉን ሀገር ጎብኝተው ይመለሳሉ። ወጣ ገባ እያሉ የሚኖሩ ሲሆኑ በስዉሩ ዓለም የሚታወቁበት ሥራ ግን ኀብስተ መናውን በመጋገር ነው። ያ ብቻ አይደለም። ደቀኛው ጠቢብ መናውን ጋግረው በደመና እየጫኑ ወደመኻል ሀገር ጭምር ይዘው ብቅ እያሉ በበረሃ ለወደቁ ምስኪኖች ትኩስ መና እየወሰዱም ያድላሉ። በዚህም "ክንፍ አልባው መልአክ" የሚል ቅጽል አላቸው። ሰማያዊ መልአክ በማለት ፈንታ ለባሴ ሥጋ መልአክ የሚል ቅጽልም ተሰጥቷቸዋል። መናውን ለመጋገር ከተሾሙ ብዙ ጊዜአቸው ነው። ተሽረው ግን አያውቁም። በእርግጥ በደቂቀ ተዋነይ ዓለም ሹም ሽር የሚባል ነገር እምብዛም ነው። አንድ ሰው ከተሾመ በኋላ ለዘለዓለሙ ሲያገለግል የመኖር እድል አለው። እድልዎ የሌለበት ዓለም ስለሆነ ለፍቅረ ሲመት የሚሣሣ ሰውም የለም። የተዋነይ ዓለም በዚህ በኩል የምድር ገነት ማለት ነው። በዚህ የተነሣ ደቀኛው በኀብስተ-መናው በኩል ከተሾሙ ድፍን ዐርባ ዓመት ሞልቷቸዋል። ሞት ፈልገው ወደመኻል እስካልተመለሱ ድረስ በሹመታቸው ይቀጥላሉ። ስለዚህ ወደስዉሩ ዓለም የሚገቡ አዳዲስ እንግዳዎች ሲመጡ ከሁሉም ከሁሉም ደቀኛው ቀድመው መፍቀድ አለባቸው።





ጓደኞቻቸው ገዳማዊው ወይራው ደግሞ ጠላ ጠማቂ ናቸው። ከየዛፉ ጉራንጉሩ ካሉ ንቦች ማር ቆርጠው የማር ወለላና ብቅል አዋሕደው በመኻል ሀገር የሌለ ጥዑም ጠላ ይጠምቃሉ። የጠላ ፍላጎት ያለው እንደልቡ ይጎነጫል። በመኻል ሀገር ሳለ የጠላ ፍቅር ያለበት ሰው ወደ ስዉሩ ዓለም ሲገባም ጠላ አይከለከልም። ወይራው ከጠመቁት ምርጥ የማር ወለላ ከመሰለ ጠላ ይጎነጫል። ወይራው በስዉሩ ዓለም ውስጥ ሰባ ዓመታትን ፋት ብለዋታል። በገዳም ስንት ዓመት እንደኖሩ ከርሳቸው በቀር የሚያውቅ የለም። ዝንጋኤ ግን ዘወር ብሎ አይቷቸው አያውቅም። እንደ ወይራ ጸንተው ሌላ ሰባ ዓመት ቢኖሩም ራሱ የሚያረጁ አይመስልም። ወይራው የተባሉትም በዚህ ምክንያት ነው። እንደወይራ ጠንካራ በመሆናቸው ወይራው የሚል ቅጽል አላቸው። ቀዳሚ ስማቸው ሊባኖስ ነበር። ወደ ስዉሩ ዓለም ከገቡ በኋላ ወይራው ተባሉ። ሊባኖስ በግእዝ ወይራው ባማርኛ ሆነ እንጅ ፈቀቅ አላሉም። ወደደቂቀ ተዋነይ ዓለም ለመግባት ሁለቱ ሰዎች ወሳኝ ናቸው። በተለይ ደቀኛው ቀላል ሰው አይደሉም። ራሳቸው ፈቅደው ካላስገቡት በቀር ትርፉ ድካም ነው። መናውን ላይጋግሩለት ይችላሉ። ከመናው ያልቀመሰ ደግሞ ከስዉሩ ዓለም ቢገባም እንደገባ አይቆጠርም። ወደ ደቂቀ ተዋነይ የመግባቱ ምሥጢር ከዚህ

ላይ ይጠናቀቃል፡፡ በሁለተኛው ቀን በተነሣው ውዝግብ ዐራት ዐይናው አጠር ያለ ንግግር አሰሙ፡፡

"ትናንት ሌሊት ከዐለቱ በር ቁጭ ብዬ የስዋሬን ቀሊልነት ስነግራቸው አደርሁ፡፡ የስዋሬው አለቃ አባተ እንዴት እንደ ተዋረደ ጭምር ነገርኳቸው፡፡ የማዳመጥ ክሕሎታቸው የወግ አይደለም፡፡ ሁለቱም በእድሜ ከሃያው መጨረሻ ከሠላሳው መጀመሪያ ናቸው፡፡ የእድሜ ክልላቸው ሰጋ ቢሆንም ብስለታቸው የጉድ ነው፡፡ ቅኔ ተምረዋል፤ መጽሐፍም ቀጽለዋል፡፡ በአእምሮ ሰከን ያሉ ናቸው፡፡ ሰብእናቸው የተረጋጋ ሰብእና ነው፡፡ ጭምቶች ናቸው፡፡ ከዛሬው ብልጭልጭ ትውልድ የተለየ እርጋታ አላቸው፡፡ በዚያ ላይ ቀለም ለመቀበል እሳት የሆነ አእምሮ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ፍቅረ ንዋይ የሚገዛው ሰብእና ይኖራቸዋል የሚል ጥርጣሬ የለኝም፡፡ ወደደቂቀ ተዋነይ ዓለም ቢገቡ ፈቃዴ ነው፡፡ ከገቡ በኋላ ምሥጢር ነጥቀው ወደኋላ ተመልሰው ወደመኻል ሀገር ገብተው ምሥጢራችንን ያወጣሉ የሚል ሐሳብ የለኝም፡፡" አሉ ዐራት ዐይናው፡፡

ደቀኛው ዐራት ዐይናው በተናገሩት ሐሳብ ደማቸው ሲገነፍል ይታያል፡፡ በዚህ ዘመን ከመኻል ሀገር የመጣ ሰውን መቀበል ሰይጣንን እንደ መቀበል ቆጥረውታል፡፡ ዐራት ዐይናው





ተናገረው ሖረ ሲቀጥሉ ከንፈራቸውን ሲወጥሩና ሲያረግቡ ደቀኛው ፈጥኖ ተቃወሙ፡፡

"እረ ተው ዐራት ዐይናው! እረ ተው ሊቁ! ዐራት ዐይና ከሆነ ሊቅ ይህንን የመሰለ አሳቤ ሲወጣ መስማትከ ያሳፍራል፡፡ ሊቅነትን ከመጠራጠርም ያደርሳል፡፡ በእርግጥ ይገባኛል! በደንብ ይገባኛል! መቼም አንተ ምሁር ስትወድ ተወዳደረ የለህም፡፡ መፍቀሬ ሊቃውንት ነህ፡፡ ቀለም የቀሰመ ሁሉ ቅዱስ መልአክ ይመስልኻል፡፡ በተለይ ቅኔ የዘረፈ ለአንተ የአብርሃም በግ ማለት ነው፡፡ እኔ ግን በዚህ አልስማማም፡፡ ገብተው ይህን መና ከቀመሱ በኋላ ወደመኻል ሀገር ሊመለሱ ይችላሉ፡፡ ወደዚያ ከተመለሱ ደግሞ የደቂቀ ተዋነይን ምሥጢር መዘክዘካቸው አይቀርም፡፡ መናውን ይዘው ከተመለሱ ደግሞ ምግብ ቤት ከፍተው ይህን የማር ሰፈፍ የመሰለ የሞት መግቻ መና እንደጉድ ሊነግዱት ይችላሉ፡፡ የእኛ ሕዝብ ደግሞ መልአከ ሞትን የሚገዝት ቆርቶ ለተለመደው የሩዝ እንጀራ ሳይቀር ይሞታል፡፡ ገና በልቶ ያልጠገበ ሕዝብ ነው፡፡ በዚያ ላይ መልአከ ሞትን የሚገዝት እንጀራ እየተሸጠ መሆኑ ከተሰማ ወረፋ አይጠብቅም፡፡ ብርቱው ደካማውን፣ ወጣቱ አዛውንቱን እየደፈጠጠ መናውን ቀድሞ ይቀምሳል፡፡ በተለይ ባለሥልጣናት ይህንን መና ለመቅመስ የሚቀድማቸው

አይኖርም፡፡ ሕዝቡን ከመናው ገሸሽ አድርገው ማንዘራቸውን ብቻ ለመናው ይሾማሉ፡፡ ከዚያም እንደሚወስኑ እኛ አናውቅም፡፡ ሲደርስ የምንረዳው ነው፡፡ ይህንን እያወቅህ ልጆች ይግቡ በማለትህ ንስሓ ያስፈልግሃል፡፡ ጨርሻለሁ፡፡" ብለው እየተጠመቁ ቁጭ አሉ፡፡

ዘር ምን ጉዳይ አሁኑ በላብ

ሦስተኛው ተናጋሪ ጠቢቡ ሖረ ነበሩ፡፡ እሳቸውም ወደደቂቀ ተዋነይ ዓለም ይግቡ ከሚሉት ክፍል ናቸው፡፡ ለተዋነይ ዓለም አዲስ ቢሆኑም ለጉባኤው ተመርጠዋል፡፡ ከወሳኞች አንዱ እንዲሆኑ የተመረጡትም አሁን ያለውን የመኻል ሀገሩን ትውልድ ጠንቅቀው ያውቁታል ከሚል እሳቤ ነበር፡፡ አስተያየት ለመስጠት ሲነሡ ሁሉም ወደ ጠቢቡ ሖረ አንገታቸውን ዘመም ዘመም አደረጉ፡፡

"አስተያየቴ አጭር ናት፡፡" ሲሉ ቀጠሉ ሖረ፡፡

"እነህ ልጆች ወደዚህ ስዉር ዓለም ሲመጡ ከመሬት ተነሥተው አይደለም፡፡ ታሪክ አጥንተው ተዋነይን አርአያ አድርገው ይመስለኛል፡፡ ተዋነይ ከዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ መልአከ ሞትን የሚገዝትበት ጥበብ ስለወረሰ እኛም እንውረስ ብለው ከመጡ እርግጥ አደጋ አለው፡፡ እኛን መስለው ለመኖር ከመጡ ግን መከልከል ያለብን አይመስለኝም፡፡ በእኔ በኩል





ከሁለቱ አንዱ ወደ ደቂቀ ተዋነይ ዓለም ቢገባ ችግር አለው አልልም፡፡ ሁለቱ ከገቡ ግን ምሥጢር ተለዋውጠው ተመልሰው ሊሄዱ ይችላሉ፡፡ አንዱ ብቻውን ከሆነ ይህንን አያደርግም፡፡ ከእኛ እንዳንዱ ሆኖ ይኖራል፡፡ በግልጽ ቋንቋ አንዱ ይግባ፡፡" ብለው ለአንዱ ፈቅደው ቁጭ አሉ፡፡

ደቀኛው ሲናገሩ ሲነሡ ገዳማዊው ወይራው ወይራ ዘንጋቸውን እየወዘወዙ በፍሥሓ ተዋጡ፡፡ የደቀኛው ደጋፊ ናቸው፡፡ ደቀኛው ከመቀመጫቸው አፈፍ እያሉ ሳለ ኃያላን ሀገራትን በጣታቸው መቁጠር ጀመሩ፡፡ አሜሪካ ፈረንሳይ ሩስያ ኢንግላድ ቻይና እስራኤል.. እያሉ ተነሥተው

"ዐረቡ ዓለም በሙሉ ኢትዮጵያን የሚወዳት ከጉሮሮ በላይ ነው፡፡ ከጉሮሮ በታች ያሏት ወዳጆቹ በራሱ ጊዜ አይተው እንደእስስት የሚለዋወጡ ናቸው፡፡ በተለይ ኃያላን ሀገራት አሜሪካ፣ ፍራንስ፣ ኢንግላድ፣ ቻይና..፡፡" ካሉ በኋላ ብዙ ሀገር የዘረዘሩ መሰሏቸው፡፡

"ሌላ ማን ቀረኝ? ሁሉንም ጠርቻቸዋለሁ፡፡ እኒህ ኃያላን ሀገራት የመናውን ምሥጢር ሲመለከቱ ሀገራችንን ይወሯታል፡፡ ከወረሯት በኋላ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመርፌ፣ በጥይት፣ በዐይጥ መርዝ፣ በጋዝ መርፌ ወዘተርፈ ሲጨርሱት ሳምንት አይፈጅባቸውም፡፡ ከታሪኩና ከገሞራው

በቀር ሌላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ደምስሰው መናውን የእጁ ያደርጋሉ። ገሞራውና ታሪኩንም መደምሰስ የማይችሉት ከመናው ቀምሰው መልአክ-ሞትን ስለሚገዝቱባቸው ነው። የተዋነይን ልጆች መግደል ስለማይችሉ ማለቴ ነው። በቀር የኢትዮጵያን ሕዝብ አፈር አልብሰው ለቀረው ዓለም በቢልዮን እየሸጡ ከመናው. እየተመገቡ ምን ያክል ዘመን መኖር እንደሚፈልጉ የሚወስኑት ራሳቸው ናቸው። ኃያላኑ። ይህንን የመሰለ የሀገር ሀብት ከመሰወር በቀር ለማንም መክሰት በእኔ በኩል ጅልነትና ቂልነት ነው። እኒህ የቅኔ ተማሪዎች አሁኑ በመጡበት እግራቸው ይሸኙ። በቀር እኔው ራሴ ፈረስ አድርጌ እሮጌው ዳንግላ ወስጄ እሸጣቸዋለሁ። ከፈለግ ፈጣሪ በዚህ ሥራዬ ከገነት ያባረኝ። ለእኔ ከማላውቃት ገነት የማውቃት ኢትዮጵያ ትበልጥብኛለች።" ብለው ስሜት ሲተናነቃቸው ጉባኤው በድንጋጤ ተዋጠ።

ጠቢቡ ሖረ ዐይናቸው በርበሬ መስሎ የደቀኛውን ንግግር ለማጠጣል ሲዳዳቸው ጠቢባኑ እጅ ከለከሏቸው።

ከዚያም ዐራት ዐይናው ነገሩን ለማረጋጋት ሰከን ብለው ተነሥተው

"በሉ ነገሩን በይደር እንምከርበት። እኔ ወደ ልጆቼ ልሂድ። ወደዚህ ዘው ብለው እንዳይገቡ መጠበቅ አለብኝ።



ወይራውም የሥራ ሰዓትም ደርሷል። ደቀኛውም መና ይጋግሩልን። ወይራውም ጠላ መበጥበጥ አለባቸው። ሖረ ከእኔ ጋር ይሂድ። ጥበቃ አለበት።" ብለው ክርክሩን ባጭር ቋጭተውት ተለያዩ። ነገስ ምን ይወስኑ ይሆን?

# ፲፰

ጥቁ ወርቁ

የጸደይ ወራት መጀመሪያ ምዕራባዊቷን ደቅ ሞሽሯታል:: የጸደይ ወር ሲፈካ ጊዜ ነው መሰለኝ ገሞራውም ተቸግሯል:: የጸደይ ወር ቅኔ ዝረፍ ዝረፍ እያለው ነው:: ነፍሱን ይማረውና በዶክተር ኄርማ ላይም በጸደይ ወራት ፍቅር ይጸናበት ነበር:: በዚህ ወቅት ነበር ለብቻው ሆኖ የፍቅር ዜማ የሚያንጎራጉረው:: ቅኔም የሚቀናው በዚህ ግሩም ወቅት ነበር:: ዶክትሬቱን አጠናቅቆ የተመረቀውም በጸደይ ወር እንደ ነበር ይታወቃል:: ዶክተር ኄርማ "ናርዶስ" ሲል በሕልሙ ይቃዥላት ከነበረችዋ ፍቅረኛው ጋር አፍላ ፍቅር የጀመረውም በጸደይ ወር ነበር:: ምን ይህ ብቻ! ስለፍቅሯ የተገረፈውም በጸደይ ወር ነበር:: ዶክተር ኄርማ ዘፈን ኀጢአት በሆነበት መንፈሳዊ ቅኔ ቤት የፍቅር ዜማ ሲያንጎራጉር የኔታ ደረሱበት:: አንተ ወሽከሬ! ዛሬስ ደግሞ ቅኔ ቤቱን ሙዚቃ ቤት ታደርገው!? በል በል እጆችህን ዘርጋ ብለው እንደ ሕጻን በለበቅ ሞሽለቁት:: የእንባ ዘለላዎች በጉንጮቹ እስኪፈሱ ድረስ እንደሕፃን በለበቅ ሲሞሸለቅ ገሞራው እንባው ዝርግፍግፍ እስኪል ሳቀ:: በለበቅ ከተገረፈ በኋላ ተናዶ ወደአዲሳባ ሲሄድ ጓዙን ሸክፎ ነበር:: ገሞራው





ገላግሎ አስቀረው:: በጸደይ ወር የመጣ ፍቅር ጽኑእ ሲሆን ዶክተር ኄርማን በግርፋት፣ ገሞራውን በቅኔ ስሜት ቀጣቸው:: ያም ሆኖ የጸደይ ወር ለሁለቱም ባለውለታቸው ነው:: ለዶክተር ኄርማ የፍቅር፣ የገሞራው የምሥጢር ወር ነው:: ዶክተር ኄርማ ስለ ፍቅረኛው በመገረፉ ናርዶስን ይበልጥ እንዲያፈቅራት ረድቶታል:: እንዲያውም በለበቅ መስተፋቅር ያደረጉለት ሁሉ መስሎት ነበር:: የተገረፈባት ለበቅ የመስተፋቅር ዕፅ እንደሆነች በመገመት ነው::

በቀስት ሲወጋ እንኳን "ናርዶስ  ሆይ!" መጨረሻዬን ባለማየትሽ እድለኛ ነሽ:: ስለፍቅር ስገረፍ ስለጥበብ ስወጋ ብታዩ ኑሮ ምን ይውጥሽ ነበር? ናርዶሴ ሆይ የእኔ ናርዶስ! አፍላ ፍቅራችንን አደራ:: ለዘለዓለም በእቅፍሽ ውስጥ አኑሪው:: ፍቅራችን አይጠውልግ" እያለ ይናዘዝ ነበር:: የፍቅር ቅኔ ባይዘርፍላትም የፍቅር ኑዛዜ ሠውቶላት ተሠውቷል:: በጸደይ ወር ጠቢቡ ሰሎሞን ሳይቀር የፍቅር ቅኔዎችን ቋጥረዋል:: በጸደይ ወር ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን "እሳት ወይ አበባ" ሲል ተቀኝቷል:: የቅኔው ሰው የፍታሔ ንጉሤ ያችን የጎጃም ጉብል መንገድ ጥሳ የተፈጥሮን ሕግ አፍርሳ እንደተዋነይ በደመና ትመጣ ዘንድ ጠርቷል::

ነይ በደመና

ነይ በደመና

"ዱሩን ጥሶ ሣሩን አጭዶ ባወጣው ጎዳና

ነይ በደመና፡፡"

ሲል በፈጣን ደመና ከጎጃም አዲሳባ ድረስ ጠርቷል፡፡ ዱሩን ጥሳ ደመና ጠቅሳ ትመጣ ዘንድ በፍቅር እንደተረታ ነግሯታል፡፡ ዮፍታሄ በደመና መሄድ እንደሚቻል የተማረው ከተዋነይ ታሪክ ነው፡፡ የዮፍታ ደመና ግን የበጋ ደመና አይደለም፡፡ ፈጣኑ የፀደይ ደመና ነበር፡፡ የፀደይ ደመና እንደ ክረምት ደመና ከባድ አይደለም፡፡ የፍቅር ደመና ነው፡፡ ምድርን በሣር፣ እንስቶችን በፍቅር ይሞሽራል፡፡ ይኸውም ሲታወቅ በፀደይ ወር ሠርግ ይበዛል፡፡ የሀገሬ እንስቶች በብዛት የሚሞሸሩት በፀደይ ወር ነው፡፡ አሁንም የፀደይ ጨረቃ ፈከታለች፡፡ የፀደይ ጨረቃ በፀደይ ወር ለሚሞሸሩ ሙሽሪታና ሙሽራው የውበት ተምሳሌ ሁናለች፡፡

ገሞራውና ታሪኩ በጸደይ ጨረቃ ላይ ዐይኖቻቸውን ሲያንገዋልሉ ቆይተው አረፍ ሲሉ ዐራት ዐይናው መጽሐፍ





ታቅፈው መጡ፡፡ ገሞራው ተቀብሎ የመጀመሪያውን ገጽ ሲገልጠው አንዲት ቃል ተመለከተ፡፡

"ወርቁን በጨለማ፣ ስታቅፈው ዘነቡ፡፡

በጥበብ ሰውሮ፣ ሳባት ወደ ልቡ፡፡" ይላል፡፡

"ሌላ ምሥጢር ሲነግሯቸው ሲሉ ምን ማለት ነው የኔታዬ?" አለ ገሞራው፡፡

ምኑ?" አሉ ዐራት ዐይናው

"ወርቁን በጨለማው ስታቅፈው ዘነቡ፤

በጥበብ ሰውሮ ሳባት ወደልቡ፡፡" ሲል ተመለከትሁ፡፡" አለ ገሞራው መጽሐፉን እየመለሰላቸው፡፡

ዐራት ዐይናው ከንፈራቸውን በምራቃቸው እየወለወሉ ዝብት፡፡

"መቼም ከመኻል ሀገር የሰማችሁት ሁሉ እውነት ሊሆን አይችልም፡፡ የስዉሩ ዓለም ሴቶች በመኻል ሀገር እንደ ሚወራው ከሰይጣን የመጡ ክፉዎች አይደሉም፡፡ ደግነታቸው ያመዝናል፡፡ ለዚህ ደግሞ የዘነቡ ታሪክ ያስረዳል፡፡" አሉ



Scanned with CamScanner

ቀለሙ ተፈራ፡፡ ፊት ለፊታቸው ካለው መጽሐፍ ላይ እያፈጠጡ፡፡ የገጹ ብዛት የትየለሌ ነው፡፡

"ዘነቡ ማን ናት? እንዴት በዚህ የጥበብ መጽሐፍ ስሟ ሊሰፍር ቻለ?" አለ ታሪኩ የዘነቡን ግጥም በጣቱ እየጠቆመ፡፡ ቀለሙ ተፈሪ የዘነቡን ሕይወት ይተርኩ ጀመር፡፡

"ስለዘነቡ መናገር አልፈልግም ነበር፡፡ ነገር ግን ከተጻፈ ላይቀር ልንገራችሁ፡፡" ብለው ቀጠሉ፡፡

"የመኻል ሀገር ሰዎች የስዉሩን ዓለም ሴቶች ስም ቢያጠፉም እነሱ ግን ለተበደለ ደሃ መፍትሔ የሚያመጡ ቸር ሴቶች ናቸው፡፡ ይኸውም በዘነቡ ታሪክ ይታወቃል፡፡ የተፈታ ትዳር መልሰው ሠርተዋል፡፡ ለደሃም ደርሰዋል፡፡ ለጭቁን ሴቶች መፍትሔ ናቸው፡፡ በአጭሩ የስዉሩ ዓለም ሴቶች በክፉ ነገር ሊጠረጠሩ ስማቸው በክፉ ሊነሣ አይገባም፡፡" አሉ ቀለሙ ወፎች ጨ..ጨ..ጨ.. ሲሉ ጀምረው፡፡

"እንዴት?" አለ ገሞራው መጽሐፉን እየዳበሰ፡፡

"ዘነቡ የአንድ ምስኪን ሚስት ነበረች፡፡ ዓመታትን በፍቅር አሳልፈዋል፡፡ መኖሪያቸው ከዚያ ማዶ ከዳንጉር ተራራ ዝቅ ብሎ ነበር፡፡ የባለቤቷ ስም ወርቄ ነበር፡፡ ራሱን ጥቂ ሲል በቅጽል ይገልጻዋል፡፡ በሀገር በምድሩ የተጠቃ (ምስኪን) ሰው





ማለቱ ነበር፡፡ ምንም ጥቁና ምስኪን ድኃ ቢሆንም ሸጋ ሚስት ነበረችው፡፡ ዘነቡ ትባላለች፡፡ ውበቷ በጨረቃ ቀመር ቢሰፈር ይሞላል፡፡ መልከ መልካም ሴት ነበረች፡፡" ብለው ከጸደይ ጨረቃ ላይ አፈጠጡ፡፡

ከዚያም "ማዶ ከገመገሙ ዝቅ ብሎ የታወቀ ሽፍታ ነበር፡፡ የወንድ ሚስቶችን ከባላቻው ክንድ እየነጠቀ ቤቱ እየወሰደ ሲያላግጥባቸው ይኖር ነበር፡፡ በየጊዜው ከዚያም ከዚያም የሚነጣጥቃቸው ሴቶች ቁጥር ከሠላሳ ከፍ ብሎ ነበር፡፡ ከሠላሳ እቁባቶቹ አንዷ ዘነቡ ነበረች፡፡ ከባሏ መንጭቆ ወስዶ ወሸማት፡፡ ባለቤቷ ከሽፍታው ጋር ለመዋጋት አቅም አጣ፡፡ በወቅቱ ሽፍቶች እንደ ልባቸው ይፈነጩ ነበር፡፡ ጃንሆይም በሽፍታ ላይ ያላቸው ሕግ ከዚህ ግባ የሚባል ሕግ አልነበረም፡፡ ሽፍቶች በየአካባቢው ሲፈነጩ "ለክፉ ቀን አርበኛ ይሆናሉ፤ ተዋቸው" የሚል አጉል ፈሊጥ ነበራቸው፡፡ አይተው እንዳላዩ ያልፏቸው ነበር፡፡ እናም ያ ልክስክስ ሽፍታ የሰውን ሚስት እየነጠቀ ሲኖር ዘነቡንም ከባሏ ላይ ነጥቆ ወሰዳት፡፡ ባለቤቷ ተናዶ ወደ ስዉሩ ዓለም ወጥቶ ከስዉሩ ዓለም ውስጥ ለዐርባ ቀን ያኽል ከዚች ውኃ ዳር እያለቀሰ ተቀመጠ፡፡ በመጨረሻ ላይ አንዲት ሴት ከስዉሩ ዓለም መጥታ አነጋገረችው፡፡ ባላገሩ ሁለመናውን ሲዘከዝክላት መሰውር ሰጥታ ሰደደችው፡፡ ሰተት ብሎ ወደ

ሽፍታው ቤት ሄደ። ቢሄድ ሴቶች እሳት አንድደው መት ተሰልፈው ሲሞቁ አገኛቸው።

ከሴቶች መካከል ግን ሚስቱ ዘነቡ አልነበረችም። ከሽፍታው ጋር ከራት ላይ ነበረች። ከሴቶች መካከል ሲያጣት ዘነቡ! ዘነቡ! እረ ዘነቡ! ብሎ ጠራት። አቤት ብላ መጣች። ተወርውሮ ሄዶ አቀፋት። ሁለቱ በቅጽበት ተሰወሩ። ይሄት ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ከዚያ በኋላ ሽፍታው ሊገድለው ቢፈልግ እየተሰወረ ሳይገኝው ቀረ። በመጨረሻ ሽፍታው ከጠላት በተተኮሰ ጥይት ሞተ። ባላገሩም በተከስቶ መኖር ጀመረ። ይህ የስውሩን ዓለም ሴቶች ቸርነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።" ካሉ በኋላ

"እንግዲህ የመልአከ ሞት መግቻው ያለው በሴቶች እጅ ብቻ ነው። እኛ ወንዶችም ከስዉሩ ዓለም ሴቶች እጅ ነው የወረስነው። ፈጣሪ ይርዳችሁ። ነገር ግን ቶሎ ተስፋ እንዳትቆርጡ። እኔ ከሴቶች ጥበብ ልወርስ እንደመጣሁ ለዐራት ዓመት ያኸል ባዶ ነበርሁኝ። በውኔ ቀርቶ በሕልሜ ሴት መጥታ አታውቅም ነበር። ቅኔ ቤት ሳለሁ ሴት በሕልሜ እየመጣች እፈተን ነበር። ከስዉሩ ዓለም ከገባሁ በኋላ ግን በውኔ ቀርቶ በሕልሜ ገጸብእሲት አይቼ አላውቅም ነበር። ይህ የስዉሩ ዓለም ቃል ኪዳን ይመስለኛል። በኋላ





ከሴቶች የመልአከ ሞትን መግቻ መና ቀመስሁ። ይኸውና እንደ ተዋነይ ሞትን ገዝቼ እየኖርሁ ነው። ወደ ፊትም እስከ ፈለግሁት ዓመት እኖራለሁ።

ጠቢባኑን እየማለድሁ ነው። እነሱ ሲማለዱ ድንገት የስዉሩ ዓለም ሴቶች ከተገለጡላችሁ ምልጃዬን አቆማለሁ። ለማንኛውም በዚሁ ደጅ መጥናት መልካም ነው። ሴቶች ቀርተው ወንዶች ከመጡ ደግሞ ያው ሞት ነው። በዚህ ዓለም ሞትና ጥበብ ጎን ለጎን ናቸው።" ብለው ቀለሙ እየተከዙ ወደ ጠቢባኑ ደቂቀ ተዋነይ ተመለሱ። ማለዳው ፈክቷል። ጥቁሩ ደመና ወገግታ አዝሏል። የናጌብ ፀሐይ ፏ ብላለች። ዐራት ዐይናው ከሄዱ በኋላ

"በዘነቡ ታሪክ እንደ ሰማነው ሴቶች በትክክል ቸር ናቸው። ለእኛም የተዋነይ አምላክ ቸር ሴቶችን እንዲጥልልን እንለምናለን። ከሴቶች ጋር የሚኖሩ ልበ-ቢስ ወንዶች ከመጡ ደግሞ ወይ ፈረስ አድርገው ሲጭኑን ይኖራሉ። በቀር ደግሞ በጦር ወግተው ወደወዲያኛው ይልኩናል።" ብለው ጸሎት አድርገው ሁለቱም ጥግ ጥግ ይዘው ከውኃዋ ዳር ጋደም ጋደም አሉ። ቀን ቀን በእንቅልፍ፣ ሌሊት ሌሊት በዐራት ዐይናው ወግ የጸደይን ወር እየገፉ ነው።

## ፲፱

### የዐራት ዐይናው ክርክር

በሣልስቱ ጉባኤው ሲጀመር በሁለቱም በኩል ውዝግብ ተንጸባረቀ። ውይይቱ ወደ ለየለት ሙግት ተገፋ።

"እነኚህ ልጆች ወደ ደቂቀ ተዋነይ ዓለም አይግቡ ማለት ተዋነይን እንደመቃወም ይቆጠራል። ሁላችንም ወደዚህ ስንመጣ ይህ ውስብስብ ችግር ገጥሞናል። እኔ ወደስዉሩ ዓለም ስመጣ ምሥጢር ቆንጥረህ ትመለሳለህ ተብዬ ከመናው ሳልቀምስ ለዐራት ዓመት ቆይቻለሁ። ደቂቀ ተዋነይ የመናውን ቁራሽ ሲመገቡ እኔ በሩቅ እየሸተተኝ ለዐራት ዓመት ቁጭ ብዬ አልቅሻለሁ። በኋላ ራሳቸው ወደ ሴቶች ስዉሩ ዓለም ወሰዱኝ። ሴቶች ከመናው ጋር አስተዋወቁኝ። እስከ ዛሬ ከዚች ንቅንቅ አላልሁም። አሁንም እኒህ ልጆች ከሴቶች ጋር ቢተዋወቁ መልካም ነው። ኀብስተ መናውን ከሴቶች መዳፍ ከወረሱ በኋላ ወደመኻል ሀገር እንዳይሄዱ እናደርጋለን። ነገር ግን ሴቶች በሌሊት ውኃ ሲቀዱ ሂደው ከተማሪዎች ጋር ድንገት ቢገናኙ ሴቶች ወደውስጥ





ይዘዋቸው ይገባሉ። ወንዶች ካገኟቸው ደግሞ በጦር ወግተው ይገድሏቸዋል። ሴቶች ካገኟቸው ደግሞ ለጊዜው በፍቅር ተስበው ይህንን የመሰለ ጥበብ ያወርሷቸዋል።

ከወረሱ በኋላ ወደመኻል ሀገር ይሄዳሉ። የዚህ ስዉር ዓለም ነገር ከዚህ ላይ ያበቃል።" አሉ ዐራት ዐይናው ያን ማደ ገመገሙን እያዩ። በተመስጦ ቃኝተው አከሉበት።

"ትዝ ይለኛል። ከዚህ ዓለም ስገባ የእኔ ምግብ ያ ማደ የዶቅማ ፍሬ ነበር። የዕለት ራቴ ከአራዊት ጋር ነበር። እንደ ዝንጀሮ የዶቅማ ፍሬ እየጠረጠርሁ ለዐራት ዓመታት ያኽል ደጅ ጠናሁ። ከዐራት ዓመታት በኋላ በጭንቅ ከመናው ቁራሽ እንድመገብ ተፈቀደልኝ። ከተፈቀደልኝ በኋላ ደግሞ መናው ከወዴት እንደሚመጣ አላውቅም ነበር። ከሰይጣን ይምጣ ከቅዱስ መንፈስ መምጫውን ሳላውቅ ለአንድ ዓመት ያኽል እንዳልተማረ ሰው አምኜ ተመገብሁት።" ለአፍታ ትንፋሽ ወስደው ሲቀጥሉ ሲሉ

"አሁን እኒህ የቅኔ ተማሪዎች ለዐራት ዓመታት ያኽል ደጅ ይጥኑ እያልህ ነው?" አሉ ደቀኛው።

"አይደለም! አይደለም! ዛሬም ያ ችግር በእኒህ ልጆች ላይ እየተደገመ መስሎ ስለተሰማኝ ነው። ተዋነይን መስለው እኛን



Scanned with CamScanner

አከለው ሲኖሩ ከመኻል ሀገር የመጡ ልጆችን እንደ ጣላት ቆጥረን መከልከሉ መልካም አይደለም:: ወደ ውስጥ ገብተው ከመናው ይቋደሱ ማለቴ ነው::" አሉ ዐራት ዐይናው ራሳቸው የተዋነይን ዓለም የተቀላቀሉበትን ዘመን ተመልሰው አስታውሰው::

ደቀኛው ሳቅ አምልጧቸው ቲ..ቲ..ቲ.. ብለው ከሳቁ በኋላ ሃሃሃ የሚል የሽሙጥ ሳቅ መረቁበት

"ዐራት ዐይናው እያረጀህ መሰለኝ! ወይም የቅኔ ተማሪ እየናፈቅህ መሆን አለበት:: የመጣውን ሁሉ ወደ ስዉሩ ዓለም ይቀላቀል የምትለው ነገር አንድም ከእርግና ሁለትም ከለው ናፍቆት የመጣ ይመስለኛል:: የደቅ ሴቶች የመልአከ ሞት መግቻውን ለመጣው ሁሉ እየሰጡ ነው:: ወደ ሴቶች ስዉር ዓለም የሚገባውን አውደልዳይ እኛ ካልተቆጣጠርነው በሴቶች ብቻ መፍረድ አይቻልም:: ሴቶች በተፈጥሯቸው ለወንዶች ርኅራኄ አላቸው:: በዚያ ላይ የስዉሩ ዓለም ሴቶች ክፋት አያውቁም:: እንደ ተዋነይ በፍቅር ለመጣ የመልአከ ሞትን መግቻ እንካ ተቀበል ነው የሚሉት:: ወደ ስዉሩ ዓለም መግባት የለባቸውም የምለው ለዚህ ነው:: እንደ ተዋነይ የሞት መግቻውን ጨብጠው ከወጡ ዓለም ዐይኑን ወደ ኢትዮጵያ ያዞራል:: ኢትዮጵያ በኃያላን መዳፍ





ትጠፍቃለች:: ይህን የመሰለ የጥበብ ዓለም እንደጎመን ቱፋ ይተረተራል:: የሚሻለው የኢትዮጵያን ምሥጢር መጠበቅ ብቻ ነው::" አሉ ደቀኛው::

"አይደለም ለመኖር እስከመጡ ድረስ መቀላቀል አለባቸው ባይ ነኝ:: እኔ ራሴ ወደዚህ ዓለም ስመጣ እርስዎን ጨምሮ በዚህ ስዉር ዓለም ይኖራል ብሎ ያመነ ጠቢብ አልነበረም:: ይኸው እስከ አሁን ከዚሁ ኖርሁ:: የተዋነይ አምላክ ተቀብሎኝ አብሬ ቀጠልሁ::" አሉ ዐራት ዐይናው በድጋሚ ሲመልሱ::

ዐራት ዐይናው እንደ ተናገሩት ወደ ተዋነይ ዓለም ሲመጡ በዚህ ይኖራሉ ብሎ ያመናቸው ፍጡር አልነበረም:: የተማሩ ስለሆኑ እንደተዋነይ ጥበቡን ጨልፈው ወደመኻል ሀገር ይመለሳሉ በሚል ጥርጣሬ ደቀኛውና ወይራው ከስዋሬው ጥበብ ጀምሮ መናውን ጭምር ነፍገዋቸው ቆይተዋል:: መናው የተፈቀደላቸው ከዐራት ዓመታት ልፋት በኋላ ነበር::

"ተው! ተው! ያለፈውን መልሰህ አታንሣ:: አንተን ወደዚህ ዓለም አትግባ ያልንህ ከሊቅነትህ ተነሥተን ነው:: ብዙ ሊቆች ወደስዉሩ ዓለም ገብተው ከመናው ቀምሰው ከመልአከ ሞት ጥርስ ከተሰወሩ በኋላ ወደ መኻል ሀገር ተመልሰው ይነጉዳሉ:: አንተም ወደዚህ የመጣኸውም በዓለም ያሉ

መሠረታዊ ትምህርቶችን አጠናቀህ ነው:: ከቅኔው ትኔ ታውቃለህ:: መጽሐፍ ቀጽለኻል:: ያ ሳይበቃህ አቡሻኸር ሳይቀር ታውቃለህ የሚል መረጃ ደረሰን:: ይህንን ሁሉ ቀለም የቀሰመ ሰው በዚህ ስዉር ዓለም ተረጋግቶ ሊኖር አይችልም:: እንደተዋነይ ወደ መኻል ሀገር ይመስላል::

ከተመለሰ በኋላ ይህንን ጥበብ መጠቀሙ አይቀርም:: ይህ ደግሞ ሀገሩን ሲያውክ የሚኖር ነገር ነው ብለን እንዳትገባ ተቃውመን ነበር:: በወቅቱ እንደተናደድህና እንደ ተበደልህ እናውቃለን:: በደልህን ተረድተናል:: ነገር ግን በወቅቱ ይቅርታ ጠይቀንኻል:: በይቅርታው ተስማምተህ ሁሉም ነገር ተሰጥቶኻል:: እንዲያውም የመናውን ቁራሽ የቀመስህ ቀን በጠና ታመህ ነበር:: እኔው ራሴ ማር መትቼ አጠጣሁህ:: ቆሎ ትምህርት ቤት ሳለህ ያሰቃይህ የነበረው ደዌ ተጎልጉሎ ወጣ:: ከዚያ በኋላ ጤና ገዛህ:: ከዚያ እስከዚህ ድረስ የደዌ ምልክት ታይቶብህ አይተን አናውቅም:: ራሴን ብለህ አታውቅም:: ለዚህ ምስጋና እንጂ ወቀሳ ማቅረብ የለብህም:: "ሙቶ የተነሣ ሕማሙን ረሳ" አሉ አበው:: ወደዚህ ዓለም ባትመጣ ኑሮ አሁን በሕይወት ትኖር ነበር? በሕይወት የመኖርህ ነገር አጠራጣሪ ነበር:: በሕይወት የኖርኸው በመናው ጠባቂነት ነው:: መናው ከመልአከ ሞት





እንዳስመለጠህ አንተም ታውቃለህ:: ሴቶችን አመስግን::" አሉ ደቀኛው ሲመልሱ::

"እሱ መቼ ጠፋኝ ብለህ ነው አባቴ ደቀኛው:: በዚያ ላይ ያቀረብሁት ወቀሳ አይደለም:: የታሪክ ማጠቃሻ ነው:: እኔ እንደተጉሳሳሁ እኒህ ሊቆች መጉሳሳት የለባቸውም ለማለት በእኔ ላይ የተፈጸመውን ግፍ መልሼ አመጣሁት እንጂ ይህኮ ወቀሳ አይደለም የእኔ ታሪክ::" ካሉ በኋላ

"እንደኔ እንደእኔ ያለምንም መጉሳሳት ወደስዉሩ ዓለም ይግቡ:: እኛን መስለው ይኑሩ:: ሊቅ መግፋት መልካም አይደለም::" አሉ ዐራት ዐይናው::

"እረ ተው አንተ ሰው! መከባበሩ ይሻላል!:: ይህ የአቡሻህር ቀለም አእምሮህን ነካ ያደርገዋል የሚሉት እውነት ይሆን እንዴ? እኔ ሳውቅህ የነገር ሰው አልነበርህም:: ዘወትር ቀለም ስታብሰለስል እንጂ ነገር ስትበላ አይቼም ሰምቼም አላውቅም ነበር:: እኒህ የቅኔ ተማሪዎች ከመጡ ወዲህ ምን እንደነካህ አልገባኝም:: ይግቡ ይግቡ የምትለው አማርኛ አልተዋጠልኝም:: ደቀኛው መግባት የለባቸውም እያሉ ነው:: እኔም በደቀኛው ሐሳብ ተስማምቻለሁ:: ከገቡ ምሥጢር ይመዘበራል ስትባል ዐይንህ አፍጥጠህ ካልገቡ ሙቼ እገኛለሁ ማለትህ ሊገባኝ አልቻለም::" አሉ ወይራው::

ዐራት ዐይናው በወይራው ንግግር "ቂቀቂ" ብለው ከሳቁ በኋላ "ወንድሜ ወይራው የአቡሻህር ቀለም እንጎልህ ላይ ወጥቷል ማለትህ አስቆኛል። የአቡሻህር ቀለም አእምሮ ያሰፋል እንጂ ናላ አያዞርም። በዚህ በኩል የሚጠረጥሩኝ ሰዎች ቂሎች ናቸው። አንተም ቂል እንዳትሆን መጀመሪያ የልቤን መምከር እፈልጋለሁ። እኔ ከተማርኳቸው የትምህርት ዐይነቶች ቀዳሚው የምርምር ትምህርቴ ይኸው የአቡሻህር ቀለም ነው። የጤናዬ ጉዳይም የተስተካከለው በአቡሻህሩ ቀለም የተነሣ ነው። ቀደም ሲል ይህንን ቀለም ሳላጠና ውስጤ ጥሩ አልነበረም። ውስጣዊ መረበሽ ነበረብኝ። የተረጋጋሁት በዚህ ቀለም የተነሣ ነው።" ብለው ያለቦታው የወደቀውን አስተያየት ወደቦታው ከመለሱ በኋላ የወይራውን ንግግር አርመው ወደጉዳያቸው ተመለሱ።

"ለእኒህ ልጆች ማድላቴ ወድጄ አይደለም። ልጆች ያለእድሜአቸው በቂ ቀለም ቀስመዋል። አዲሳባ ቢሄዱ የዕለት ራት አያጡም። ሁለቱም የአብነት መምህራን ስለሆኑ ከአንዱ ደብር ተቀጥረው መኖር ይችላሉ። ነገር ግን ያንን ሕይወት እንዳልወደዱት ተረድቻለሁ። ገሞራው የሚባለው አጭሩ ሲጀምር ከተሜነት ደመኛው ነው። ፊቱም ገጠሬ ነገር ነው። አማርኛውም ከከተሜዎች ጋር የሚስማማ አማርኛ አይመስልም። ንግግሩ ከባድ ነው። በዚያ ላይ ሲብሰለሰል ነው





የሚውለው። ታሪኩም ከጎንደር በቀር የሚያውቀው ሌላ ዓለም የለውም። ጎንደርን ደግሞ በድፍኑ ከተማ ለማለት እቸገራለሁ። መካነ ቅርስ እንጂ የድረስ ድረስ ብልጭልጭ ከተማ አይደለችም። መካነ ቅርስ ናት። መካነ ሲቃውንትም ጭምር። እንዲያውም የዋልድባ መነኮሳት ጎንደርን ከዋልድባ የበለጠች ገዳም ናት ሲሉ ይወራረዳሉ። ለምን መሰላችሁ? በዚህ ዘመን ዘመናዊ ከተማ የሚባሉት ባሕር ዳር፣ ሐዋሳ ናዝሬትና አሁን ድረስ በዘመናዊ መልኩ እየተገነቡ ያሉ ብልጭልጮች ናቸው። ጎንደር ግን የቅርስ ከተማ ናት። ታሪኩም የኖረው በዚች ከተማ ሲሆን ከከተማዋ ውበት ይልቅ ቅርሶቿን ጠንቅቆ ያውቃቸዋል። እኒህ ልጆች ወደዚህ ሲመጡ ትልቅ ራእይ እንዳላቸው መገመት ደግሞ ቀላል ነው።" አሉ ዐራት ዐይናው።

"ጅብ እስኪነክስ ያነክስ ነው! አሁን የሚቅለሰለሱት ይቺን የመና ቁራሽ በእጃቸው እስኪያስገቡ ድረስ ነው። ከዚያ በኋላ ተለውጠው አውሬ ነው የሚሆኑት። በሩቅ መከላከል ነው ጥሩ።" አሉ ደቀኛው። ጠቢቡ ሖረ ቀስ ብለው መናገር ሲጀምሩ ደቀኛው በጽሙና ተከታተሏቸው።

"እኔ ወደዚህ የመጣሁት በቅርቡ ነው። እስከ ቅርብ ቀን መኻል ሀገር ስለነበርሁ ያለውን የኑሮ ዘይቤ በከፊል



Scanned with CamScanner

አውቀዋለሁ፡፡ ዘመኑ በከፊል የርኩስ መንፈስ ዘመን ነው፡፡ አንድዬ መዓቱን ካላቀለለልን የመኖር እጣ ፈንታችን የሲያል ዕጣ ፈንታ እየሆነ መጥቷል፡፡ ከዚህ የተነሣ ትውልዱ አገሬ አውጪኝ እያለ ሀገሩን መልቀቅ ይፈልጋል፡፡ ከዚህ ተነሥቼ ግምቱን ማስቀመጥ እችል ይመስለኛል፡፡ እኒህ ሊቆች ወደዚህ ቢገቡ ተመልሰው ወደ መኻል ሀገር የሚሄዱ አይመስለኝም፡፡ የመኻል ሀገሩ ችግር ችግራቸው እንደሆነ ተረድተዋል፡፡ መኻል ሀገሩ የቀጣፊዎች መናኸሪያ ሁኗል፡፡ የተረጋጋ ኑሮ የሚኖሩት በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪው ሰው ሰኞ በትካዜ፣ ረቡዕ በፍሥሓ ዓርብ በድንግርግር ኑሮውን የሚገፋ ነው፡፡ ትክክለኛ የአብነት ሊቅ የሆነ ሰው ደግሞ ዘመን የወደደውን መስሎ መኖር አይችልበትም፡፡ እኒህም ከቅኔ ቤት የተፈለቀቁ የወርቅ እንክብሎች ናቸው፡፡ ከብልጭልጩ ዓለም ያልተነካኩ ከጭቃ ውስጥ የተገኙ አልማዞች ናቸው፡፡ ከጭቃ ውስጥ የተገኘ ወርቅ ከጭቃው የሚሳተፈው ነገር የለም፡፡ ጭቃው አልማዙን ሊዋሐደው እንደማይችል እኒህንም ተማሪዎች ብልጭልጩ ዓለም ገና አልተዋሐዳቸውም፡፡ ስለዚህ ባጭሩ እኛን መስለው ይኑሩ፡፡ ከመናው ይቅመሱ፡፡ ደቀኛው እባክዎ ይማለዱን፡፡" አሉ በዐይናቸው እንባ መልቶ፡፡





“በዚህ በኩል የምማለድህ አይመስለኝም፡፡ ለማንኛውም ነገሩ በጥብቅ ይጠና፡፡ ደግመን ደጋግመን እንምከርበት፡፡ ይህ ሰዉር ዓለም የእኔ ብቻ ዓለም አይደለም፡፡ የኢትዮጵያውያን ጥምር የነገ ተስፋ ነው፡፡ የጠቢባን ዓለም ደግሞ ጥንቃቄ ይፈልጋል፡፡ በዚህ ውስጥ ያሉ ሕያዋን ጠቢባንን ጨምሮ አያሌ የጥበብ መጻሕፍት አሉ፡፡ እኒህ ወዳሉበት የሚገቡ ሰዎች በጥብቅ መመርመር አለባቸው፡፡ ዘው ብለው የገቡ ሰዎች ዘው ብለው ሊወጡ ይችላሉ፡፡ ተዋነይ በዚህ ዓለም ሳለ ጥሩ የቀለም ሰው ነበር፡፡ ጥበቡን ተጠቅሞ አምልጦ ከዚህ ከወጣ በኋላ መልአከ ሞትን ለሰባት ዓመት ያኽል ስለገዘተ ጠንቋይ ተብሎ ስሙ ተሰበረ፡፡ ያ ሰባራ ስም ለእያንዳንዱ ሊቃውንት ተራ በተራ ታደለ፡፡ ተከፋፈለ፡፡ ከዚያ ወዲህ ያለውን ውሽብስብ ሁላችሁም ታውቃላችሁ፡፡ ትውልዱ ጥንቆልናን ከፍልስፍና ለይቶ ከማወቅ ደረጃ ገና አልደረሰም፡፡ ያ በነገሠበት ዓለም እኒህ ሊቆች ከገቡ በኋላ ቅንጣት ፍልስፍና ይዘው ወደመኻል ሀገር ቢመለሱ ምን እንደሚከሠት ገምቱ፡፡ ሀገሪቱ ሙሉ በሙሉ ትበረቀሳለች፡፡ ባዕዳን በረቀቀ መሣሪያ እየመረመሩ ባዶ ነው የሚያደርጓት፡፡ ይህን የተዋነይ ዓለም ያገኙ እየመሰላቸው እንደ ቅርጫ ሥጋ ይከፋፈሏታል፡፡ ስለዚህ እኒህ ተማሪዎች በመጡበት እግራቸው ወደመኻል ሀገር ይመለሱ፡፡ በቀር አንዱን ፈረስ

አድርጌ መኻል ሀገር ወስጄ እሸጠዋለሁ፡፡ ሁለተኛውን እኚህ አድርጌ ለድኃ በነጻ እሰጠዋለሁ፡፡ ድሃ ጭኖ ጭኖ ጀርባው ሲመለጥ ለጅብ ይሰጠዋል፡፡ ከዚህ ሁሉ ግባጣ ግን ወደመኻል ሀገር ሸኛቸው አባቴ ቀለሙ፡፡ ጨርሻለሁ፡፡" አሉ ደቀኛው የምር ተበሳጭተው፡፡

"እኔም ተስማምቻለሁ፡፡ በዛሬው ሌሊት ወደመኻል ሀገር ይመለሱ፡፡" አሉ ወይራም ተደርበው፡፡

ዐራት ዐይናው ቀለሙ እጅግ ተናደው ለሁለቱ ምላሽ ሳይሰጡ እንደ ተለመደው በውስጣቸው "አቡነ አቡነ አቡነ ዘበሰማያት" እያሉ ወደ ነታሪኩ ተመለሱ፡፡ ጉባኤው ለውሳኔ ተሰብስቦ ያለ ውሳኔ ተበተነ፡፡

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)





# ፳

የኩሽ ሴቶች

ዐራት ዐይናው በደቀኛው ተበሳጭተው በወይራው ተናደው ወደ ሁለቱ ባለቅኔዎች ሲደርሱ ጀንበር ተሸኝታ ነበር፡፡ ለሁለቱም የእግዜር ሰላምታ ከሰጡ በኋላ ስለስዉሩ ዓለም ታሪክ በጨረፍታ ያወጓቸው ጀመር፡፡ ተስፋ እንዳይቆርጡ አልፈው አልፈው መተረኩን ተያያዙት፡፡

"ይህ ዓለም ክልኤ ዓለም ነው፡፡" አሉ ድንግዝግዝ ባለው ምሽት፡፡ የጸደይ ወራት ጨረቃ እስክትፈካ እየጠበቁ፡፡

"በመኻል ሀገር ቅኔ ቤት ሳላችሁ ክልኤ ዓለም መኖሩን መቼም ሳትሰሙ አትቀሩም? ሁለት ዓለማት ማለት ግን የሴትና የወንድ ዓለም ማለት አይደለም፡፡ የቅዱሳንና የጠቢባን ዓለም ማለት ነው፡፡" አሉ

"አዎን! በትክክል ሰምተናል፡፡" አለ ገሞራው፡፡

"እንዴት ነበር የሰማኸው?" ቀለሙ ተፈሪ መልሰው ጠየቁት፡፡

"በዚህ ውስጥ ሁለት የስዉራን ዓለማት እንዳሉ ትኔ ቤቱን የረገጠ ሁሉ ያውቀዋል፡፡ በተለይ የተዋነይን ታሪክ እስከጥጉ ላጠና አዲስ ታሪክ አይደለም፡፡

ወሬው በየገዳማቱም ይወራል፡፡ በጣና ውስጥ ባሉት በመንዳባ፣ በእማማ ገዳም፣ በክብራን፣ በዳጋ፣ በጣና ቂርቆስ በጣራ፣በምጽሌ ዘወር ዘወር ስል ስለዚህ ሥፍራ በሚገባ ሰምቻለሁ፡፡ እንዲያውም በዳጋ የተዋነይ ዓለም ከአበያ እስከ በልያ አገው ምድር ድረስ ነበር እያሉ በሰፊው ይተርካሉ ገዳማውያኑ፡፡ ይህ ትርክት የሚነሣው ደግሞ ዝም ብሎ አይደለም፡፡ የታሪኩ ዱራ ከዳጋው ጻድቅ አቡነ ኂሩተ አምላክ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ የአቡነ ኂሩተ አምላክ የገዳም ቅፈፍ (ወሰን) ከአበያ እስከ በልያ ነበር ይላሉ ገዳማውያኑ ሲተርኩ፡፡ አበያ ማለት ጎጃም ውስጥ ከሞጣ ዝቅ ብሎ የሚገኝ ሸለቆ ቢጤ ነው፡፡ በማዶ በኩል በጌምድር ያዋስነዋል፡፡ ለጎንጅ ቆለላ ቅርብ ነው፡፡ ጎንጅ ደግሞ የተዋነይ መንደር መሆኑ መቼም ይታወቃል፡፡ አበያ በረሓ ተዋነይ ሱባኤ ይገባበት የነበር ቆላ ቀመስ ሸለቆ ሲሆን በልያ ደግሞ ያ ረጅም ተራራ ነው፡፡ በልያ ተዋነይ በደመና እየተጫነ መጥቶ ያርፍበት እንደነበር በአፈ ታሪክ ይነገራል፡፡ ከበልያ ተነሥቶ ከዚሁ ስዉር ዓለም ሲደርስ ሴቶች ይቀበሉት እንደነበር በየቅኔ ቤቱ ወሬው ይሰሰቃል፡፡ ከሴት መንፈስ ጋር ጋብቻ ፈጽሞ ነበር የሚባለው





ከዚህ ዓለም ሴቶች ዘንድ በመመላለሱ ነው፡፡" አለ ከርታተው ገሞራው በቅኔ ቤትና በገዳም ሲንከራተት ከቀሰማቸው አፈ ታሪኮች እየጠቃቀሰ፡፡

"ታሪኩ ከሞላ ጎደል እውነት ነው፡፡" አሉ ዐራት ዐይናው ከአንደበቱ ተቀብለው፡፡

"እኔም በመጀመሪያ እንዳነሣሁት ደቅ ክልኤ ዓለም አለው፡፡ የመጀመሪያው ዓለም የጠቢባኑ ደቂቀ ተዋነይ ዓለም ሲሆን በጠቢባኑ ጎን ለጎን ለነፍሳቸው ያደሩ ቅዱሳን ጭምር አሉበት፡፡ አንዳንድ ቀን ለጠቢባኑ ጭምር ይገለጣሉ፡፡ ፈጣሪያአቸውን በከበሮ ሲያመሰግኑም ይሰማሉ፡፡ ቅዱሳን ያ..ው ቅዱሳን ናቸው፡፡ በመኻል ሀገር ያሉ ገዳማውያን ወደዚህ የሚመጡት ከእኒህ ቅዱሳን ለመባረክ ነው፡፡ በእነሱ ቋንቋ ፍልሰት ይሉታል፡፡ በዳጋ፣ በጣና ቂርቆስ፣ በተድባበ ማርያም፣ በማኅበረ ዶጌ፣ በዋልድባ ያሉ አበው መባረክ ሲፈልጉ ወደዚህ ዓለም ይመጣሉ፡፡ ተባርከው ወደገዳማቸው ሲመለሱ መንገድ ላይ ወይም እንደሺንፋ ባለ በረኻ ገብተው ያርፋሉ፡፡ በእነሱ ቋንቋ ፍልሰት ማለት ይህ ነው፡፡ እኒህ ገዳማውያን ከቡራኬው በኋላ የሥጋ እረፍት እንጂ የሞት መግቻውን አይፈልጉም፡፡ ስለዚህ ወደዚህ ሲመጡ ያለምንም

ክልካይ ይገባሉ። ተባርከው ወደወደዱት በዓት ተመልሰው ያርፋሉ።

"በመጀመሪያው ዓለም ያሉት የእኔ ቢጤዎች ደቂቀ ተዋነይ የሚባሉት ግን ከየቅኔ ቤቱ ተውጣጥተው ከመኻል ሀገር ወደዚህ የመጡ ናቸው። ደቂቀ ተዋነይ መባላቸው ተዋነይን አብነት አድርገው ጥበብ ፍለጋ መጥተው ኀብስተ መናውን ቀምሰው በሕይወት የሚኖሩበት ስለሆነ ነው። የወል ስማቸው ሐሽማል ይባላል። በቅኔ ቤት ቋንቋ ከርታታ ኮከቦች በመባል ይታወቃሉ። መልአከሞትን ገዝተው የሚኖሩት እነኚህ ናቸው። ይህንን ቅኔ ቤት በተደጋጋሚ ሰምታችሁታል።" ካሉ በኋላ እያዋዙ ተነተኑት።

"ደቅ ክልኤ ዓለም ነው። የኩሻውያን ሴቶችና የኢትዮጵያውያን ወንዶች ዓለም ተብሎ ይከፈላል።" ብለው የሚጠሩ ሰዎች ጥቂት ግንዛቤ ያጥራቸው ይመስለኛል።

"ሁለተኛው ዓለም ደግሞ ስዉሩ የሴቶች ዓለም ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ባንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ዓመት ኩሻውያን መጥተው እንደ ሰፈሩበት ይነገራል። አብዛኞቹ ሴቶች ነበሩ። የስዉሩ ዓለም ቃል ኪዳን ለሴቶች የተሰጠ ቀዳሚዎች እኒህ ሴቶች ስለሆኑ ነው። እኒህ ሴቶች ባለትዳሮች ነበሩ። ተሰውረው እየኖሩ በሕግ አግብተው





ይወልዱ ነበር ይባላል። በእርግጥ ከሴቶች ጋር ያሉ፣ ነገር ግን በተፈጥሮ ይሁን ወይም በሌላ ምሥጢር ከሴቶች ጋር ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ባንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ዓመተ ዓለም በዚህ የተገኙ ልበ ቢስ ወንዶች ነበሩ። በቅኔ ቤት ቋንቋ "እንቡዘ ልብ" ሲባል ትሰሙ እንደነበር አውቃለሁ።" አሉ ዐራት ዐይናው ቀለሙ ተፈሪ።

"ብትክክል" አለ ገሞራው።

"የሚገርመው ደግሞ ወንዶች ልበ-ቢስ መሆናቸው ነው። የስዉሩ ዓለም ወንዶች ከሴቶች አንጻር ፈዛዛዎች ናቸው። ይህን ነገር ሴቶች በጥበብ ያደረጉት ይመስለኛል። ወንዶች ከስዉሩ ዓለም ወደ ገሀዱ ዓለም እየወጡ ሴቶችን እንዳያስቸግሯቸው ልበ ቢስ ያደረጓቸው ይመስለኛል። በእርግጥ አሁን ላይ ልበ ቢሶች ከዚህ ዓለም እየወጡ እየሞቱ አልቀዋል። አሁን የቀሩት ለዘር ያኽል ጥቂቶች ናቸው። እኒህን ለመመርመር ሞክሬ ውሉን ሳገኘው አልቻልሁም። ወንዶችን እንዳልጠይቃቸው ልበ ቢሶች ናቸው። ከሴቶች እንዳልረዳ ምን አልባት ሴቶች በጥበብ ልበ ቢስ አድርገዋቸው ከሆነ ብዬ ፈራሁ። ስለዚህ በዝምታ አልፌዋለሁ። ስለልበ ቢስ ወንዶች ጥያቄ ብታነሡ ዝምታ ነው መልሴ።" ብለው የልበ ቢስ ወንዶችን ነገር ከደመደሙ በኋላ ቀጠሉ። ገሞራው

አቡኑም ምሥጢር ሲጣፍጣቸው ተመስጠ ሲከጅላቸው ዐይኖቻቸውን የጨፈኑ ይመስሉ ነበር፡፡

"አንዳንድ የዘመኑ ተመራማሪዎች እንደሚሉት የሙሴ ሚስት ከእኒህ ወገን ትሆን ይሆን?" አለ ታሪኩ

"በቅዱስ መጽሐፍ ሙሴ ከኢትዮጵያ ሚስት እንዳገባ ተጠቅሷል፡፡ ሙሴ ለሚስትነት የመረጣት ሴት ግን የስዉሩ ዓለም ሴት መሆኗ አልተረጋገጠም፡፡ በእርግጥ የሚመሳሰል ነገር አለ፡፡ ሙሴ በምድረ በዳ መና ከደመና ወርዶለት ይመገብ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይተርካል፡፡ በዚህ ስዉር ዓለምም ኅብስተ መና አለ፡፡ ነገር ግን የስዉሩ ዓለም መና ከሰማይ የወረደ መና አይደለም፡፡ ከዚህ ስዉር ዓለም የተገኘ መና ነው፡፡ ከደቅ ሴቶች እጅ፡፡ በእርግጥ የመናውን ቁራሽ ምሥጢር ጨርሼ አልናገረውም፡፡ ለእናንተ አዲስ ባይሆንም ጊዜው ገና ነው፡፡ ወደ ውስጥ ለመግባት ጠቢባኑ መፍቀድ አለባቸው፡፡ ስለ እሱ ደግሞ እየመከርን ነው፡፡ ጠቢባኑ ምሥጢር ጨልፈው ይሄዳሉ ብለው በሙሉ ልብ አልፈቀዱም፡፡ ክርክር ላይ ነን፡፡ ለኅብስተ መናው እንደመጣችሁ ግልጽ ቢሆንም አሁን ላይ ጊዜው ሸጋ አይደለም፡፡" ሲሉ ገሞራው ፈጥኖ ተቃወመ፡፡





"የለም! የለም! ካሁን በኋላ ወደመኻል ሀገር መመለስ አንፈልግም፡፡" አለ ገሞራው፡፡

"ለምን?"

"እኔ ኑሮ አይቸግረኝም፡፡ ከጫጫታ በቀር ያተረፍሁት የለም፡፡ መኻል ሀገር ሳለሁ ያልረገጥሁት ምድር የለም፡፡ ኢትዮጵያን በከፊል አውቃታለሁ፡፡ ሴላው ቀርቶ ለሰው ልጆች ተስማሚ አየር አለው ከሚባለው ዋና ከተማችን አዲሳባ ጭምር ለተወሰነ ጊዜ ቆይቻለሁ፡፡ የወፍ ዝማሬ ስፈልግ የመኪና ጡርንባ ጆሮዬን እየበሳው ኑሬአለሁ፡፡ ከዚህ ግን የወፎች ዝማሬ ብቻ በቂዬ ነው፡፡ በዚህ መኖር እፈልጋለሁ፡፡ ከፈለገ ወንድሜ ታሪኩ ወደ ጎንደር ተመልሶ ማስተማር ይችላል፡፡ ራሱን አስመስሎ የሚቀርጻቸው ሊቆች ቢኖሩ እመርጣለሁ፡፡ ከጎንደሩ ክፍለ ዮሐንስ ቅኔ ቤት ገብቶ ቢያስተምር እልፍ አእላፍ ሊቆችን እንደሚፈጥር ጥርጥር የለውም፡፡ እኔ ግን ወደመኻል ሀገር ድርሽ አልልም፡፡ በዚህ ዓለም ሞት ዘበት ቢሆንም የጥበብን ጭራ ይዤ ስሄድ እሞታለሁ፡፡ ነፍሴ ከሀገር በቀል ጥበብ ጋር ትውጣ፡፡" አለ ገሞራው

"እረ ምን በወጣኝ እያ! እኔም ፍላጎቴ በዚሁ ስዉር ዓለም መኖር ነው፡፡" አለ ታሪኩ



Scanned with CamScanner

"ለማንኛውም ይህ በሁለታችሁ ብቻ የሚወሰን ውሳኔ አይደለም፡፡ ለጊዜው አንዳንድ መጽሐፍ ላይ ጥናት አድርጉ፡፡ እየቆየን እንወስናለን፡፡ አሁን አፍላ ፍቅር ላይ ስለ ሆናችሁ ስጨሩ ዓለም አዲስ ስለሆነባችሁ እንጂ ጥቂት ቆይቶ መኻል ሀገር ሊናፍቃችሁ ይችላል፡፡ እሱንም አስቡበት፡፡" ብለው ክፋሉን ከተረኩላቸው በኋላ፡፡

"ጠቢባኑ ከፈቀዱ ትገባላችሁ፡፡ በደቂቀ ተዋነይ ዓለም አብረን እንኖራለን፡፡ አሁን ግን ወደኋላ እንመለስ፡፡ ከዚህ ማለፍ ክልክል ነው፡፡ የተዋነይን ውኃ የጠጣ ከዚህ ድረስ ይፈቀድልታል፡፡ ወደ ዋናው ዓለም ለመቀላቀል ጊዜው ገና ነው፡፡ ክርክር ላይ ነኝ፡፡ ወደ ኋላ ተመለሱ፡" ገሞራውንና ታሪኩን ወደ ኋላ መልሰው ዐራት ዐይናው ወደፊት ገሰገሱ፡፡ ገሞራው አሻቦ የመሰለ ጥርሱን እያስተማመ ወደኋላ ተመለሰ፡፡ ታሪኩም ዐይኑን ቶሎ ቶሎ በእጁ ያሸዋል፡፡ የዐይኖቹ የጠጉር ጭራዎች ተነቅለው ሊያልቁ ደርሰዋል፡፡ ለሁለቱም የጸደይ ወር መልካም ወር አይደለም፡፡





# ፳፩

## የወይራው ይቅርታ

እነሆ የደቂቀ ተዋነይ ዓለም በጉም ተሸፍኗል፡፡ ከጉሙ በላይ ያለው የደመና ጥጥ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የተዘረጋ የደብተራ ሻሽ ይመስላል፡፡ ደቀኛው የሚጋግሩት የመናው መዓዛ ከሩቅ ይሸታል፡፡ በውስጡ የሚርመሰመሱ አራዊት ፈጣሪያቸውን በዝማሬ እያመሰገኑ ነበር፡፡ ጠቢባኑ ደቂቀ ተዋነይ በየጉራንጉሬው ተወትፈው የእሰቱን ጸሎት ይሰልቁታል፡፡ ከወፎች ዝማሬ በቀር የሰው ድምፅ አይሰማም፡፡ ድቅድቅ ባለው ሀገር የተመሰጉት እኒህ የጥበብ ሊቆች ዘለዓለማቸውን ያሸለቡ ቢመስሉም ከሞት ጋር ቃል ኪዳን የላቸውም፡፡ ያለፈቃዳቸው በአጠገባቸው ሳይዞር ሞት ተወግዟል፡፡ እንደ ዐራት ዐይናው ከቅኔ ቤት፣ እንደ ወይራው ከገዳም፣ እንደጠቢቡ ሖረ ከመንከራተት፣እንደ ደቀኛው ከክልኤ ዓለም የመጡ ሊቆች ያለፈውን ትዝታ እያነሡ ሲያወጉ የደራሲ ብዕር ያስመዠልጣሉ፡፡ ኅሕ ሲቀድ የእነ ገሞራውን ጉዳይ ለመወሰን ለዐራተኛ ጊዜ ተሰበሰቡ፡፡ የዛሬውን ጉባኤ ባርከው የከፈቱት ቀለሙ ተፈሪ ሲሆኑ ቀዳሚው ተናጋሪ ግን ደቀኛው ነበሩ፡፡ በመኻል ሀገር ሊቆች ዘንድ መና ከደመና ያወርዳሉ እየተባለ ይወራ ነበር፡፡



Scanned with CamScanner

ወደመኻል ሀገር ብቅ ሲሉ የቅኔ ተማሪዎችን ትኩስ እንጀራ ጋግረው ሲያበሉ ታይተዋል ይባላል:: ግን ምን ያደርጋል! ጥቂት ሳይቆዩ ይሰወራሉም እየተባለ ይወራላቸዋል-ደቀኛው::

"በተዋነይ ዓለም ካላችሁት አበው መካከል ከርታታው እኔ ነኝ:: ከዚህ ዓለም ወደ መኻል ሀገር በየጊዜው ተንከራትቻለሁ:: ወደመኻል ሀገር ስሄድ ደግሞ የማርፈው በየቅኔ ቤቱ ነው:: እንግዳ ሁኜ ወደ ቅኔ ቤት ጠጋ ባልሁባቸው ጊዜያት ከቅኔ ተማሪዎች አንደበት የተለያዩ ጸያፍ ነገሮችን ሰምቼ አውቃለሁ::" ብለው እንደ ወረደ ለመናገር ጥቂት አመነቱ::

"ከሰማኋቸው አስቀያሚ ነገሮች የመጀመሪያው የቅኔ ተማሪዎች ተዋነይን የሚያውቁት በሊቅነቱ ሳይሆን በጠንቋይነቱ ነው:: ተዋነይ ከተነሣ የንጉሡን ሚስት በፍቅር ማርኮ በአስማት ሰውሮ ደቅ እንደወሰዳት በዚያም ዓለሙን ሲቀጭ ኑሮ እንዳለፈ በስፋት ይተርካሉ:: ዋሸራ ቅኔ ቤት ጎራ ባልሁበት ሰዓት አንድ ወጣኒ ተማሪ

"እኔ የተዋነይን አስማት ባገኝ እንደ ሰሎሞን ሰማኒያ ዕቁባት እንዲኖሩኝ እፈልጋለሁ::" ሲል ሰምቼ አዝኛለሁ:: ይህን የሰማሁት ከዐሥር ዓመታት በፊት ነው:: ከዐሥር ዓመታት በፊት የማዕበል ፈንቴን የሕይወት ታሪክ ለማጥናት





እንከራተት ነበር:: እኔ ከርታታው በዚህ አዝኛለሁ:: በአንጻሩ ደግሞ ሊቅ ሊቅ ዘራፊዎች ዐይቼ ደስ ብሎኛል:: ያ ተማሪ ተመላልሶ ቅኔ ቤት ገብቶ እንጂ ኢአማኒ ሊሆንም ይችላል::

..በዘጠና ስድስት ዓመተ ምሕረት ደግሞ ባሕር ዳር ቅኔ ቤት ጎራ ብዬ ነበር:: የቅኔ መምህሩ ቀጭን ሊቅ ሲሆን የቅኔ ነበልባል የሚተፋ አንደበት ነበረው:: የባሕርዳር ቆነጃጅት በቅኔ ቤቱ በኩል ሲያልፉ ተማሪዎች አንገታቸውን ወለም እስኪላቸው ዘወር ዘወር እያሉ ሲያፈጡ አይቶ

"ፍቅረ ሥጋ ጠሊ መርዓት ዘአንደደክሙ::

በነጽሮ የጎልፍ ለክሙ::"

ብሎ ዘለፋ ቅኔ አወረደባቸው:: በመጨረሻም ተማሪዎች ከፍትወት ወጥተው ቅኔው ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ ማስጠንቀቂያ አዘል ምክር ሲሰጥ ሰምቻለሁ:: ምን አለፋችሁ! ጠቅለል ሲል ያሁኑ ትውልድ. ተዋነይን መሆን የሚመኘው ለሥጋዊ ፍላጎቱ ብቻ ይመስለኛል:: ከላይ ከላይ ለእናት ሀገሬ የአቅሜን እሠራለሁ የሚሉ ሁሉ ቃሉን የሚጠቀሙት ለሽንገላ ነው:: በደቂቀ ተዋነይ ዓለም ደግሞ ጥበብ ቆንጽሎ የሚሄድ ሰው እንዲገባ አይፈለግም:: እኒህ ልጆችም ወደዚህ ሲመጡ የቻሉት ከተዋነይ ጥበብ ቆንጥረው ወደመኻል ሀገር

ተመልሰው በሥጋ ለመክበር እንጂ ለመኖር አይመስለኝም። የውስጣቸውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ቢሆንም ሰምና ወርቁ ግልጽ ነው። ከዕለት እንጀራ አያልፍም።" አሉ ደቀኛው።

ደቀኛው ተናግረው እንዳበቁ ተራው ወደሑረ ተሳለፈ። የዛሬው የጉባኤው መሪ ዐራት ዐይናው ሲሆኑ ለሌሎች ቅድሚያ እየሰጡ ነው። ለመናገር እንዳልቸኮሉ ገጻቸው ይናገራል። ጠቢቡ ሑረ ተፈቅዶላቸው ለመናገር ሲነሡ ዐራት ዐይናው ገጻቸው ፈካ።

"እኔ ለደቂቀ ተዋነይ ዓለም የመጨረሻው ሰው ነኝ። ለስዉሩ ዓለምም እንግዳ ነኝ። በመኻል ሀገር ሳሉ ቅኔ ቤቶች ግን እኔ እቀርባለሁ።" ብለው ወደ ደቀኛው ዘወር አሉ። ደቀኛው በንግግራቸው ደስተኛ እንዳልሆኑ ገጻቸው ይናገራል። ነገር ሳይቀበሉ ሲቀሩ ከንፈራቸውን ያወጫምዳሉ። አሁንም ሳያውቁት ያንን ትእምርት እየሠሩ ነበር።

"ከባሕርዳር ዙሪያ ደቀኛው ያነሡትን ሊቅ እኔም አውቀዋሁ። ከቅኔ ቤት ጀምሮ ነው የማወቀው። ቅኔን በእሱ ልክ የሚያውቀው የቅኔ ሰው አለ ለማለትም ያዳግታል። ነበልባል ነበር። ባሕር ዳር ዙሪያ ቅኔ ማስተማር ሲጀምር ቀዳሚው ተማሪ ሁኜ ከመወድሱ ተሳትፌአለሁ። ቅኔ ቤቱ ሲመሠረት





የመጀመሪያውን ጎጆ የቀለስሁት እኔው ራሴ ነኝ። በሳምንት ውስጥ በመቶ የሚቆጠር ተማሪ ከተማውን አጥለቀለቀው። በአካባቢው የነበሩ ባላገሮች ከተማሪው ብዛት የተነሣ ድንጋጤ ተፈጠረባቸው። አንዳንድ ተማሪዎች ከሴት ፍቅር ጋር የተየያዘ መወድስ መዝረፍ ሲጀምሩ አይቶ ከነጽሮ ብእሲት ያለፉ መሰናክል ውስጥ እንዳይገቡ ፈልጎ

"ፍቅረ ሥጋ ጠሊ ብእሲት ዘአንደደክሙ።

በነጽሮ የኀልፍ ለክሙ።" ሲል አስጠነቀቀ። ስድ ትርጉሙ

"ፍቅር ያነደዳችሁ ልጆቼ ሆይ! በፍትወት መጎምጀቱን ተውት።

ፍቅር በነጽሮም ያልፋል።"

ሲል መወድስ መዝረፉ ግልጽ ነው። የቅኔው ዜማ ልክ የዋዜማ መድፊያ ነበር። እንግዲህ በዚያ ወቅት የነበሩ ተማሪዎች ከተማ ገብተው በፍቅር ቢነደፉ አይገርምም። ያ ማለት ግን ለፍቅር ሲሉ የተዋነይን ጥበብ ሲፈልጉ ይኖራሉ ማለት አይደለም። ወደዚህ የሚመጡ የቅኔ ተማሪዎች ደቂቀ ተዋነይን መስለው መኖር ሊሆን ይችላል። ስለዚህ እኒህን መቀበል ያስፈልግ ይመስለኛል።" ሑረ የሚያውቁትን ተናግረው እንደ ፈጸሙ ወይራው ከወይራ ከዘራቸው ጋር



Scanned with CamScanner

ተነሡ:: ከንዴታቸው ብዛት የተነሣ ገጻቸው ጢስ የጠጣ ገላ መስሏል::

"እኔ ወይራው ሖረ በተናገረው ማመን አልፈልግም:: ማገም የፍየል እረኛ በቅኔ ተማሪ ስም መጥቶ ወደተዋነይ ዓለም ገብቶ ምሥጢራችንን ነጥቆ ወጥቶ ሀገራችንን አደጋ ሲያደርስባት በሕይወቴ ማየት አልፈልግም:: ከዚህ ከተዋነይ ዓለም ወጥቼ ወደ ገዳሜ እመለሳለሁ:: ጉም ኢየሱስ ገብቼ ሞቴን እመርጣለሁ:: ከዚህ ዓለም ውስጥ መልአከ-ሞት ስለማይገባ እንጂ አሁኑ ከዚች ከፊታችሁ ድፊት ብዬ አፈር ብቀምስ ፍላጎቴ ነበር:: አዎን! ከዚች እስከ ጉም ኢየሱስ ድረስ ሩቅ አይደለችም:: ከዚች ወጥቼ የሞት ጽዋዬን እጨልጣለሁ:: ከዛሬ ጀምሮ የመናውን ቁራሽ መቅመሴን አቆማለሁ:: ከዚያም ነገ መንገድ እጀምራለሁ:: ሞት ናፍቆኛል እሄዳሁ::" አሉ እያማረሩ::

"የለም! የለም! እሱ የማይጥም ንግግር ነው::" ሲሉ ጀመሩ ዐራት ዐይናው::

"ሞት አውርድ ማለት አስፈላጊ አይደለም:: በቅዱስ መጽሐፍ የታዘዘው ይች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ነበር:: በግሌ ሞት የለመኑ ሰዎች አሟሟታቸው ሲከፉ ተመልክቻለሁ::" ሲሉ ጀምረው ነገሩን ለማለዘብ አንድ ገጠመኝ አመጡ::





"መኻል ሀገር ሳለሁ ገዳም ለገዳም ዞሬያለሁ:: ይህ የገጠመኝ ግን ጮለሚት ማርያም በምትባል ገዳም ውስጥ ነበር:: በገዳሙ ውስጥ በምናኔዋ የምትመካ መነኩሲት ነበረች:: ከምናኔዋ ጎን ለጎን ግእዝ ተምራ ውዳሴ ማርያም ደገመች:: ቅኔም ቆጠረች:: ቅኔውና ምናኔው ሲሠምራላት ትዕቢት ቢጤ አደረባት:: ከሴቶች ጋር በሴት አንቀጽ ቁማ ስታስቀድስ ቄሶች ግእዝ ሲሰሳቱ እንዲህ በለው! ውሽልክ! ውትፍትፍ! እያለች ማረም ጀመረች:: ይህ በዚያ ቀርቶ በእመይቴ ገላነሽ ሀገር ታይቶ ተሰምቶ አይታወቅም:: የቅኔዋ እመቤት ገላነሽ እንኳን ግእዝ ሲሰሳቱ ቄሶችን አንጓጣ አታውቅም ነበር:: ይቺ ግን ሲቅነቷ፣ ምናኔዋ፣ትዕቢቷም የጉድ ሆነ:: ቄሶች አዘኑባት:: መቋሚያ ዘቅዝቀው የረገሟትም ነበሩ:: ይህ አልበቃ ብሎ በመጨረሻ ሰይጣን በፍትወት ይፈትናት ጀመር:: ከመሰናከሏ በፊት ፈጣሪ ሞት እንዲያመጣባት ሱባኤ ገብታ ለመነችው:: ከዚያ በኋላም ምኑን እነግራችኋለሁ! በገዛ እጇ ሞት ለምና የሞት ፊት አውራሪዎች ባንድ ጊዜ ተሸንድጉደው ወደ ውስጧ ገቡ:: ደረቷን ብርድ አነደዳት:: ሳንባዋ ከጉሮሮዋ ተወተፈ:: ወባ ጠመደቻት:: መራመድ ተሳናት:: ሞት በለመነች በሦስት ዓመቷ እስከ መጨረሻው አሸለበች:: አባቴ ወይራውም ጉም ኢየሱስ ገብቼ ሞቴን እቀበላለሁ ያሉት ንግግር ለደቂቃ

# ፳፪

ቢሰውር

በነጋታው ሌሊት ዐራት ዐይናው ቀደም ብለው ከተፍ አሉ። የስዋሬውን ቀሊልነት ተንትኖ ለማስረዳት እያሰላሰሉ ነበር አመጣጣቸው። ታሪኩና ገሞራው ተነሥተው እጅ ነሥተው ተቀበሏቸው። ከሁለቱ ሊቆች ዋሽ እንደ ደረሱ እንደ ሕፃን ልጅ ጥቅልል ብለው ከልሙጥ ድንጋይ ሥር ተወሸቁ። ወንበር እያለ ልሙጥ ድንጋይ ላይ ማረፋቸው ትሕትና ለማስተማር ነው። የቅኔ ተማሪ ቅኔ-ዘራፊ ከሆነ በኋላ ትዕቢቱ አይጣል እንደሆነ ያውቃሉ። የትዕቢቱን ጫፍ ቅኔ ቤት ሳሉ ጠንቅቀው ያውቁታል። ሰውን እንደ እንስሳ ከሚቆጥሩ ትዕቢቶች ጋር ባንድ አብረው በልተዋል። ባንድ መጽሐፍ አንብበዋል። ያንን ያውቁ ስለነበር ያ የትዕቢት መንፈስ ምን አልባት ተከትሏቸው ከመጣ በማለት ትሕትና ለማስተማር ያለምንም ወንበር ሽብረክ አሉ። ገሞራው በአንክሮ ተመለከታቸው። ሊቅነታቸው ሳይገድባቸው ውስጣቸው በትሕትና ሲሰበር ዐይቶ የእሱም ውስጣዊ ልቡናው ተቀለጠመ። ገሞራው የጥርስ ሕማሙ ብሶበታል። አፉ መርዝ የተሞላ ምራቅ እየተፋ ነበር። ታሪኩም ቢሆን ዐይኑን በድሪቶ አስሮ መዋል ጀምሯል።





ነፋስ ሲነካው ያንገበግበዋል። ቀሪ ምሥጢራቸው እድሜ እንዲቀጥሉላቸው ዐራት ዐይናውን በተስፋ መጠበቅ ብቻ ነበር።

"ይህ መጽሐፍ ስለ ስዋሬ ዘርዘር አድርጎ የሚናገር መጽሐፍ ነው። የከርታታ ኮከቦችን ውጣ ውረድ ይዟል። ከፊል ታሪካቸው የተከተበው በዚህ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ በዚህ በስዉሩ ዓለም ይኖራል። የተለያዩ ሊቃውንት የእጅ መድበል ነው። ወደ ተዋነይ ዓለም የገባውም ቀደም ባለው ዘመን ነው። መጽሐፉ በመኻል ሀገር እንዳሉ መጻሕፍት ስርዝ ድልዝ የለውም። በውስጡ የስዋሬን ወጎች ሰብስቦ ይዟል። በየገጹ ገጠመኝ ተጽፈውበታል። በመድበሉ የተካተቱ ተአምር የሚመስሉ ጥበባት በተራቀቁ ሊቃውንት እንደተፈተሹ ይነገራል። ወደዚህ ዓለም ያመጣው አንድ ተማሪ ነበር። ይህን ዓለም ተሳልሞ ወደመኻል ሀገር ተመለሰ። በስዉሩ ዓለም ዐሥር ዓመታት ኑሮ ወደመኻል ሀገር ከተመለሰ በኋላ ይሙት ይዳን ግን መረጃ የለኝም። በዚህ መጽሐፍ እኔ የማውቀው የስዋሬ ታሪክ ጭምር ተካቷል። መጽሐፉ ዳር ከጥበቡ በቀር ወጎዎች ተጽፈዋል። አስማቱ ግን ተፍቋል። አስማቱ የተፋቀው በዚህ ስዉር ዓለም አስማት ስለማይሠራ ነው። ስዉሩ ዓለም የቅዱሳንና የጠቢባን ዓለም ስለሆነ የሰይጣን ኮቴ የለበትም። ተሰውሮ

እንዳይኖር ስጨራት ያዩታል:: ተረጋግቶ እንዳይኖር የቅዱሳኑ ጸሎት ያቃጥለዋል:: ሰይጣን ወደዚህ ስዉር ዓለም የማይገባው ለዚህ ነው:: ሰይጣን ከሌለ ደግሞ አስማት መኖሩ አስፈላጊ አይደለም:: ስለዚህ አስማቱ ተፍቋል:: የከርታታ ኮከቦች የሕይወት ውጣ ውረድ ግን ይኸው አለ:: ከአስማቱ በቀር ወተ ቢኖር ምንም ችግር የለውም ብለን ይዘነዋል::" በደስታ ተውጠው ያብራሩ ጀመር::

"ወተ በግጥም ይጀምራል:: እነሆ ግጥሙ!

"ላንተስ ይበቃኻል ሞፈሩ ቀንበሩ::

አብነትስ ለእኛ ለደቀ መዝሙሩ::"

ይላል ብለው ቂቂቂ እያሉ አከሉበት:: በዚያ የሀብታም ምጣድ በሚያክለው የመጽሐፉ ዐምድ ላይ ከዚች ግጥም በቀር ምንም ቃል የለም:: አስማቱ ሲፋቅ ግጥሟ ለብቻዋ ቀርታለች:: ከስዋሬው ምሥጢራት አንዱ የተከተበት ምሉእ ገጽ ነው:: ስለ እሱ እንነጋረን::" ዐራት ዐይናው እንዲህ ናቸው:: በል ሲላቸው ስለከርታታ ኮከቦች ተርከው አይታክቱም:: ራሳቸውም በሐሳብ ይንከራተታሉ:: ከስዉሩ ዓለም ቁጭ ብለው አንዳንድ ጊዜም በአካል ወደመኻል ሀገር ብቅ እያሉ የሀገር ምሥጢራት ይፈትሻሉ::





ጓሺ! የኔታ!" አለ ገሞራው::

"መጀመሪያ ሰው በሦስት ነገር ይሰወራል:: እነሆም ቦታ፣ አስማት፣ የተፈጥሮ ጥበብ ናቸው:: እኒህ ሁላ የመልአከ ሞት መግቻው አብሮ ከሌላቸው ከንቱ ናቸው:: ለጊዜው ያማልላሉ:: ሲቀርቧቸው ግን ጉም እንደ መጨበጥ ይቆጠራሉ:: ትነት ብቻ ናቸው:: ለዚህ ነው ስዋሬ ብቻውን አያዛልቅም የምለው::" ብለው ይተረትሩት ጀመር::

"እንግዲህ በመጀመሪያ እንዳነሣሁት ከመልአከ ሞት መግቻው በቀር የስዋሬው ምሥጢር በመኻል ሀገርም አልፎ አልፎ ነበር:: በጊዜው ስመኻል ሀገር ሊቆች መሰወርን ያስተማራቸው ነበልባሉ ተዋነይ ሲሆን እሱ ሲያልፍ ተከታዮቹ ገፍተውበት ነበር:: ነገር ግን እንደተዋነይ የሞት መግቻው ስለሌላቸው ተስፋ እየቆረጡ ተውት:: ተዋነይ ግን የመናውን ቁራሽ ከስዉሩ ዓለም ይዞ ወደጎንጅ ስለሄደ መልአከ ሞት እንዳይነካ ከመናው በከፊል ጋግሮ ይቀምሳል:: መልአከ ሞት በመጣት እግሩ ይመለሳል:: እንዲህ እንዲህ እያደረገ እስከ ሰባት ዓመት ኖረ:: ይህ ሰባት ዓመት መልአከ ሞትን የገዘተበት ዓመት ሲሆን የተዋነይ መላ እድሜው ግን በውል አይታወቅም:: ራሱ ፈቅዶ ወድዶ በቁሙ ትቢያ እስኪሆን ድረስ የፈለገውን ያኽል ዓመት ሞት ሳይነካው



Scanned with CamScanner

እንደልቡ ኑሯል፡፡ ነገር ግን የጥበብ አባታችን ተዋነይ ከስዋሬው በቀር የመልእክ ሞትን መግቻ ምሥጢር ለማንም ገልጦት አያውቅም፡፡ ከስጪሩ ዓለም ወደመኻል ሀገር ወስዶ ለራሱ ብቻ ይጠቀምበት ነበር እንጂ፡፡ መሰውሩን ግን በፀሐይ በጉባይ በየጊዜው አድርጎታል፡፡ እርግጥ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ተዋነይ ሲሰወር ቢደንቅም በጊዜው የቅኔ ሊቆች ማመን ተስኗቸው ነበር፡፡ ስዋሬውንም እንደተራ ወሬ ቆጥረውት ነበር፡፡ ከተዋነይ በኋላ የመምህራን የዘር ሐረግ የመጨረሻው ሊቅ ሲደግመው እየጎላ መጣ፡፡ እኔም ማመን የቻልሁት ከዚያ በኋላ ነው፡፡ በመጽሐፉ ዐምድ የተከተበው ግጥምም የተዋነይ ተከታይ ስዋሬን የተቀላቀለ ቀን የተደረሰ ግጥም ነው፡፡ ከዚያ በኋላ እኔም እንደአቅሜ ያንን መመርመር ጀመርሁ፡፡ ስመረምር ዓመታት አለፉ፡፡ ዘመናት ከነፉ፡፡ ዐይኖቼ መፍዘዝ ጀመሩ፡፡ እውነታውን ሳረጋግጥ ዳክሬ ዳክሬ አንድ ሊቅ መጽሐፉን ወደዚህ ዓለም አመጥቶት ከእጄ ገባ፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ መጽሐፉ ከእጄ ወጥቶ አያውቅም፡፡ ዘወትር ሳነበው አዲስ ይሆንብኛል፡፡ እንግዳ ድርሰት! ነው፡፡" በእጃቸው ስለያዙት ግዙፍ መጽሐፍ ውስተ ውሳጤ ተርከው ዝም ሲሉ

"ስዋሬን ያረጋገጠው የቅኔ ሊቅ ማን ይባል ነበር? በእናንተ ጊዜኮ የቅኔ ሊቆች እልፍ አእላፍ ነበሩ፡፡ እስከ ደርግ ዘመነ መንግሥት በየቅኔ ቤቱ ወፌ ሰማይ የቅኔ ዘራፊዎች ነበሩ፡፡





እየከሰሙ የመጡት ከደርግ ዘመን በኋላ ነው፡፡ በደርጉ ዘመን ሊቆች እየታፈሱ ለጦርነት ተማግደዋል፡፡

ከደርግ ውድቀት በኋላም ደግሞ ኢማእምራን እየታፈሱ ተሹመዋል፡፡ ተማሪው ማን ነበር ነው ያሉት?፡፡" አለ ታሪኩ

"ቢ..ቢ..ሰ..ው..ቢሰውር! ቢሰውር ይባላል፡፡ በእርግጥ ከዚያ በፊት ስሙ ተከስተ ነበር፡፡ ቆንጆዋ አብነትን ከሰወረ በኋላ ቢሰውር ተባለ፡፡ ለእኔም የቅርብ ጓዴ ነበር፡፡ ጎንደር ቅኔ ቆጽሏል፡፡ ዋድላ መወድስ ዘርፏል፡፡ ከጊዜ በኋላ ጎጃም ገብቶ ጎንጅ ቅኔ ቤት ተገናኘን፡፡ ከእኔ ጀምሮ ከእልፍ አእላፍ ተማሪዎች ጋር ፍቅረ ቢጽ መሠረተ፡፡" ሲሉ ጉድ መዘዙ፡፡ ገምራውና ታሪኩ በትርክቱ ፈዝዘው ምን ሊያመጡ ነው እያሉ ያዳምጧቸው ነበር፡፡

"እንግዲህ በወቅቱ የቅኔ ዘራፊዎችን ጨምሮ ሁሉም የአብነት ተማሪዎች በእንተ ማርያም እያሉ ይኖሩ ነበር፡፡ ተማሪዎች በእንተ ማርያም ሲሉ አልፎ አልፎ ከባላገር ጋር መጋጨት ደግሞ አዲስ አይደለም፡፡ እኔም ሆነ ቢሰውር መንደር ለበእንተ ማርያም ስንሄድ ባላገሮች ዝናም የምትገዝቱ እናንተ ናችሁ እያሉ በቆላ ከዘራ ያዳክሩን ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን ቢሰውር ቲም በቀሉን ተወጣ፡፡" አሉና በወጉ ሊቀጥሉ ስለፈለጉ ከንፈራቸውን በምራቃቸው አራሱ፡፡

እንደ ማዘዣ ገደል የጠበበች ከንፈራቸውን በምራቅ አለስልሰው ጉሮሯቸውን ስለው ከዘራቸውን ተደግፈው በማብራራቱ ገፉበት፡፡

"ከዕለታት አንድ ቀን ጓደኛዬ ቢሰውር በእንተ ማርያም ለማለት ወደመንደር ሄደ፡፡ በእንተማርያም ሲል ከባላገር ጋር ጠብ ገጠመ፡፡ ባላገሩ በቆላ ከዘራ እስኪበቃው ወቃው፡፡ ደሙን እያዘራ ወደቅኔ ቤት ተመለሰ፡፡ ለዓመታት የስዋሬውን ጥበብ ለማግኘት ተንከራተተ፡፡ ከዓመታት በኋላ የስዋሬው ነገር በእጁ ገባ፡፡ ወደቅኔ ቤት ተመለሰ፡፡ በዚች ሌሊት ስዋሬውን ፈትኖ ሲያረጋግጥ ወደባላገሩ ቤት ሰተት ብሎ በኩራት ከተፍ አለ፡፡ ከበሩ ሲደርስ መሰወሩን ተጠቀመ፡፡ ቢሰውር ዘው ብሉ ወደባላገሩ ቤት ሲገባ ከትንፋሹ በቀር የእግሩን ኮቴ ጭምር ሰውሮት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ የኮቴ ድምፅ አልነበረም፡፡ ጥላ አልባ መሰውር ነበር የያዘው፡፡ ተሰውሮ እንደገባ የባላገሩን ልጅ እጅ ለቀም አደረጋት፡፡ ሲጨባበጡ እሷም እንደእሱ ተሰወረች፡፡ ቢሰውር በስዋሬ በኩል የተዋነይ ልጅ ሆነ፡፡ ከዚህ ላይ ተዋነይን ልብ ይሏል፡፡" ብለው የቢሰውርን ታሪክ ገታ አድርገው ተዋነይን በምናብ ከፊታቸው ቁጭ አድርገው መግለጹን ቀጠሉ፡፡





"መኻል ሀገር ዘወር ዘወር ስል ይህ ትኩሱ አዲስ ትውልድ ተዋነይ ማን ነው? ሲል በጥያቄ ያጣድፈኝ ነበር፡፡ ልብ አውልቁ ብዙ ነው እማይደል?! ያም ያም ልቤን ያወልቀው ነበር፡፡ ተዋነይ ማን እንደሆነ ለማስረዳት ቃላት በቂ አይደሉም፡፡ ተዋነይን በትክክል ለመግለጽ ሥራውን መመልከት ነው፡፡ የጎንጅ ሊቆች በፀሐይ በጉባይ እንደነገሩን ተዋነይ በተሰወረች ውኃ የተቀሰፈ አእምሮ ይፈታ ነበር፡፡ ከመሬት አንሥቶ ቅኔ ያዘርፋል፡፡ በፍየል ሥጋ አጣፍጦ አጉርሶ የቅኔ ሊቅ ያደርጋል፡፡ ብዙዎች ከመሬት ተነሥተው የተራቀቁት በዚያች ውኃ ነው፡፡ ይህን ሲያደርግ ከተፈጥሮዋ ውኃ በቀር ሌላ ምናምንቴ አይጨምርም፤ አይቀንስም ነበር፡፡ በውኃዋ ተማሪውና እንኳ ቅኔ እንደ ዘረፉ ሲተረክ ይኖራል፡፡ የሴት ቅኔ አዋቂዎች የመጡትም ከተዋነይ እኅት ወዲህ ነው፡፡ የመጀመሪያዋ የሴት የቅኔ ሊቅ የተዋነይ እኅት ናት፡፡ አደይ ትባላለች፡፡ አደይ ማለት በትግርኛ ቋንቋ እናቴ ማለት ነው፡፡ 'አደይ ማርያም' እንዲሉ የአስመራ ልጆች፡፡ እናቴ ማርያም ሲሉ፡፡ ወደ ሴቶች የቅኔ ምሥጢር ስንመጣ በመጀመሪያ አደይ ቅኔ ዘረፈች፡፡ ከዚያ በኋላ የሴት ባለቅኔዎች ተኮለኮሉ፡፡ እንደክረምት አግቢ ተፈለፈሉ፡፡ ከእኒህ እንስት ባለቅኔዎች መኻል ቀዳሚዋ የቅኔ ሊቅ ገላነሽ ትባላለች፡፡ የቅኔ እመቤት ነበረች፡፡ የቅኔ ቤቱን በር ለረገጠ ሁሳ ስሟ አዲስ አይደለም፡፡

የቅኔ ሊት መሆኗንም ማስተዋስ አያስፈልግም:: ባልብ ያለን ሰው መልሶ ማስታወስ ቂልነት ነው:: በተለይ እንደ እኔ ካሉ የቅኔ ሊቃውንት አይጠበቅም:: እመይቴ ገላነሽ እንደ ሀገር ሴት ናት:: ነገር ግን ምሥጢር ናት:: ምሥጢረኛ ሴት ሳትሆን ራሷ ምሥጢር ናት:: ባለቅኔዎች ኢትዮጵያዊቷ ሖሜር ይሏታል:: ባለቅኔነቷን ለመግለጽ ሖሜር ድረስ ተወርውረዋል:: ግሪክ ወርደዋል:: ሖሜር ግሪካዊ ባለቅኔ ሲሆን ገላነሽ ኢትዮጵያዊት ባለቅኔ መሆኗን መደጋገም ለቀባሪ ማርዳት ነው:: ያን ለመግለጽ ሖሜርን ፍለጋ የገሰገሱ ብዙ ናቸው:: ምሳሌ ቢያጡላት ግሪክ ድረስ ወርደው ምሳሌ አመጡላት:: በሰማይ መልአክ እንዳይመስሏት የሴት መልአክ የለም:: ጭራሽ በቅኔም በኩል መልአክ አይደርስባትም:: ተራው መልአክ ቀርቶ ሊቀ መላኩ ራሱ የቅኔ ሊቅ አይደለም:: የቀለም ሊቅ ለገላነሽ የሚሰጥ ቅጽል ነው:: ሊቅነቷን ለማነጻጸር ግሪክ ወርደው ምሳሌ ፈለጉላት:: እኔ ግን ከሖሜር ይልቅ አሜር ቢሏት ደስ ይለኝ ነበር::" አሉ ዐራት ዐይናው ተዋነይና እመይቴ ገላነሽ ትዝ ብለዋቸው::

"አሜር ማለት ፀሐይ ማለትም አይደል?!" አለ ታሪኩ::

"አዎን! አሜር ማለት ፀሐይ ማለት ነው! ለፀሐይ ትልቁ መሳፍርት የሌላቸው ጨረሮች አሏት:: ለባለ ቅኔዋ ገላነሽም





ከአገዝ ያለፉ፣ ከቀመር የተረፉ መወድሶች አሏት:: በወግ በወጉ ቢከተቡም ኑሮ በዐሥር የሚቆጠሩ ዳጎስ ዳጎስ ያሉ መጻሕፍት ይወጣቸው ነበር:: በእኛይቱ መንደር ግን ይህ አልተለመደም:: ባለቅኔ የረከሰባትን፣ ቀጣፊ የገነነባትን ኢትዮጵያ ታቅፈን ሀገሬ ሀገሬ ማለቱን ከእውቀት ቆጥረነዋል:: እንደ ተዋነይ መልአከ ሞትን ብንገዝት እንደ ቢሰውር ከጠላት ፊት መሰወር ብንችል ምንኛ እንደምንሸልል ኣላውቅም:: ትምክሕታችን ተነግሮ አያልቅም ነበር::" ብለው ወደቢሰውር ታሪክ ተመለሱ::

"ከቢሰውር በቀር ራሱን በስዋሬ የገለጠ ሊቅ አሁን ላይ በመኻል ሀገር ያለ አይመስለኝም:: ቢኖርም ዜናው ጎልቶ አይነገርም:: የተሰውረ ሰው የመናው ቁራሽ ከሌለው ከስድስት ቀን በላይ የመኖር እድሜ የለውም:: ያ በመሆኑ ስዋሬው እየመነመነ መጥቷል::" ሲሉ ከመኻል ሀገር የነበረው ስዋሬ መክሰሙን ከተነተኑ በኋላ

"ተዋነይ እንደተሰወረ ቢሰውርም ከባላገሩ ቤት ሲደርስ ተሰወረ:: ተሰውሮ ዘው ብሎ ሲገባ የባላገሩ ልጅ ወጥ እየሠራች ነበር:: አለላ የመሰለች ሴት ልጅ ማዕድ ቤት ወጥ ስታማስል ተሰውሮ ገብቶ እሷንም ወደእሱ በጥበብ ስቦ

ሰወራት። ሁለቱም በስዋራ ዓለም ተያዩ።" ሲሉ ታሪኩን እንደ ውኃ ፉት ሲሉት

"እኔ አላምንም።" ገሞራው በድንግዝግዝ ጠየቃቸው።

"አዛኚቷን! ስልላችሁ! ስሟን ሳይቀርኮ ነገርኋችሁ። ማን ነበር አያ ያልኋችሁ?" ብለው ስዋራው በትክክል መሠራቱን በስሟ ለማረጋገጥ።

"ማን ነበር ስሟ አያ!" ዐይናቸውን ጨፍነው መፈለግ ሲጀመሩ መጣላቸው።

"አዎን እ.. እ...! አ..ብ..ነ..ት..ይባላል። የተዋነይ ልጅ በአብነት ላይ መሰወሩን ሲደረግመው ከአባቷ እይታ ውጪ ሆነች። ወጥ እየሠራች ባማታውቀው ዓለም ከነፈች። በትክክል ተሰውራ ነበር። የመሰወሯ ምሥጢር የገባት የምትሠራው ወጥ ከእሷ እይታ ውጪ ሲሆን ነበር። ታማስለው የነበረው ወጥ ከመዓዛው በቀር ድስቱ ጠፋባት። ምድጃው ተሰወረባት። እሷ ተሰውራ እንጂ ምድጃውማ ቦታውን ለቅቆ ወዴትም አልሄደም። ወጡም ሆነ እሷ ለጊዜው በቦታው ነበሩ። ቢሰውርና አብነት በሌላ ዓለም ነበሩ። አብነት በማታውቀው ዓለም ሰጥማ ስትቃብዝ አንድ ሲቅ





ከፊት ለፊቷ ቆሞ በፍቅር ዐይን ነደፋት። በፍቅር በመነደፏ በስዋራ ውስጥ እንዳለች መረዳት ከለከላት።" ካሉ በኋላ

"በእርግጥ ቢሰውርን ከዚያ በፊት ታውቀዋለች። በቅኔ በኩል አንቱ የተባለ ወጣት ሲቅ ነበር። ድምፀ-መልካም ሲቅ። በስዋራው ጊዜ የፍቅር ዐይኑን ሲያንገዋልልባት ማመን አልቻለችም። ድሮም ለፍቅር ትመኘው ስለነበር በፊቱ ስታልፍ ጉልበቷን ብርክ ይይዘው፣ ፍቅር ያብረከርካት ነበር። አሁን ግን ሰተት ብሎ ገብቶ ከፊቷ ገጭ ብሎ ይባስ አብረከረካት። በተለይ በስዋራ ውስጥ መሆኗን በጆሮዋ ሹክ ሲላት ደስፈቅ አላት።" አሉ ቀሰሙ ተፈሪ።

"እንኳን ተሰውራ ድሮም የሔዋን ልጆች ለፍቅር ይኸው ናቸው። ቦታ ከተመቻቸው በአፍታ ያፈቅራሉ። የኋላውን በአፍታ ይረሳሉ። ወደፊት ይቀጥላሉ።" ታሪኩ ተባበራቸው። ዐራት ዐይናውም ቀጠሉ።

"እናላችሁ አብነትን ሰውሮ በፍቅር አክንፎ ከቤቷ አውጥቶ ወደ ቅኔ ቤት ይዟት ከተፍ አለ። ወዲያው ከስዋሬ ወደተክስቶ ተመለሰች። ከዚያ በኋላ ከቢሰውር ጋር በፍቅር መኖር ከጀላት። ከባላገር የቆላ ዱላ ተላቃ የሲቅ ሚስት መሆን ወዴት ሊገኝ? በፍቅር እፍአለች። በሁለቱም ልብ ፍቅር ሰመረ። ያ ባላገር ግን ልጁ ወዴት እንዳለች ሲያውቅ

አዋቂ ፈልጎ አስተረጎመው። አብነት ግን ከእጁ ወጥታ የሊቅ ሚስት ልትሆን ተቃርባ ነበር።" ካሉ በኋላ በግጥሙ ምሥጢር ጥቂት ፈገግ ማለታቸው አልቀረም። በአግባቡ ፈገግ ብለው

"ከዚህ ላይ ቅኔውን ልብ በሉ። የልጇ ስም አብነት ነው ብያለሁ። ስሟ ከቅኔው ጋር ቅኔ ሆኗል። ጥንቱን አብነት የሊቆች ጥበብ ነው። ከባላገር የሌለ፣ ባንዳንድ ሊቆች መዝገበ ጥበብ ብቻ የሚገኝ በየጊዜው የማይሸሻል ነገር አብነት ይባላል። ወዲህም ትምህርት በአእምሮ ተቀርፆ ለዘለዓለሙ እንዲቀር የሚያደርግ ነገር በሙሉ አብነት ይባላል። የቢሰውር ጓደኞች 'አብነትስ ለእኛ ለደቀ መዝሙሩ' ያሉት በሰምና በወርቅ ነው። ሰሙ ድሮውም አብነት የደቀ መዝሙር ነው ማለት ሲሆን ወርቁ ደግሞ አብነት ከእነሱ ያንዱ ፍቅረኛ መሆን መቻሏን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። እንግዲህ ይህን ያመጣሁት በስዋሬ የመኖርን ምሥጢር ቀለል አድርጋችሁ እንድትረዱት ፈልጌ ነው። በስዋሬ መኖር ይቻላል ስንል አንዳንዶቹ ተረት ተረት ይመስላቸዋል። ተረት ግን አይደለም። እውነት ነው። በእርግጥ አሁን ዘመኑ ዘመነ ድንግዝግዝ ስለሆነ ይህንን መቀበል ከባድ ነው። በጨለማው ዘመን ድንግዝግዝ ዓለም ተወልዷል። በዚህ ድንግዝግዝ ዘመን ድንግዝግዝ ትውልድ መፈጠሩ ደግሞ የታወቀ ነው።